የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፳፭
አዲስ አበባ መጋቢት ፰ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

26th Year No. 25
ADDIS ABABA 17th March, 2020

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፹፮/፪ሺ፲፪ ዓ.ም
የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ……………....ገጽ ፲፪ሺ፪፻፸፰

**Content**

Proclamation No. 1186/2020
The Excise Tax Proclamation ……Page 12278

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፹፮/፪ሺ፲፪

## የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ

የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸውን ዕቃዎች ዓይነት እንደገና በመፈተሽ በትክክል የቅንጦት ዕቃዎች ናቸው በሚባሉ፣ የኅብረተሰቡን ጤና በሚጎዱ እና የማኅበራዊ ችግር በሚያስከትሉ እንዲሁም መሠረታዊ በመሆናቸው ምክንያት የገበያ ተፈላጊነታቸው በማይቀንስ ዕቃዎች እና አገልግሎቶች ላይ እንዲጣል ማድረግ በማስፈለጉ፤

በማምረቻ ወጪ ላይ ሲሰላ የነበረው የኤክሳይዝ ታክስ በፋብሪካ የመሸጫ ዋጋ እንዲተካ መደረጉ ታክስ ከፋዮች ሊከፍሉት በሚገባ ታክስ ተገማችነት ረገድ ሲያጋጥማቸው የነበረውን ችግር የሚያቃልል መሆኑ ስለታመነበት፤

በሥራ ላይ የነበረው የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ባሉበት ጉድለቶች ምክንያት የኤክሳይዝ ታክስን በትክክል በመሰብሰብ ረገድ ያጋጠመውን ችግር መቅረፍ የሚያስችል አዋጅ ማውጣት ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) እና (፲፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

PROCLAMATION No. 1186/2020

## EXCISE TAX PROCLAMATION

**WHEREAS,** it has become necessary to review the type of goods on which excise tax has been collected and impose the tax on goods and services that are believed to be luxury, hazardous to health, causes social problems as well as on basic goods which are demand inelastic;

**WHEREAS,** it is believed that replacement of the current excise tax which was assessed on production cost by ex-factory price will alleviate the problem encountered by taxpayers due to lack of predictability on the amount of tax they are liable to pay;

**WHEREAS,** to overcome the problems encountered in collecting proper excise tax due to shortcomings in the current excise tax proclamation, it has become necessary to introduce a new law that puts in place a system which alleviates problems so far encountered;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55(1) and (11) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows.



www.chilot.me

## ምዕራፍ አንድ

## ጠቅላላ

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፹፮/፪ሺ፲፪" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ:-

፩/ "አውሮፕላን" ማለት ሰዎችን ወይም ዕቃዎችን በአየር የሚያጓጉዝ ማናቸውም ዓይነት ማጓጓዣ ነው፡፡

፪/ "ግንኙነት በሌላቸው ሰዎች መካከል የሚደረግ ግብይት" ማለት በሁለት ሰዎች መካከል በትክክለኛ የገበያ ዋጋ የሚደረግ ግብይት ነው፡፡

፫/ "ለሰው አገልግሎት የማይውል" ማለት በመጠጥነት ለሰዎች አገልግሎት እንዳይውል ተደርጎ የተሠራ ነው፡፡

፬/ "የአልኮል ማጣሪያ ፋብሪካ" ማለት አልኮል ለማምረት ፈቃድ የተሰጠው ፋብሪካ ነው፡፡

፭/ "የጉምሩክ ቀረጥ" ማለት በገቢ ዕቃዎች ላይ የተጣለ የጉምሩክ ቀረጥ፣ ሱር ታክስ ወይም ሌላ ተመሳሳይ ቀረጥ ነው፡፡

፮/ "የተፈቀደለት የዕቃ መጋዘን" ማለት የታክስ ባለሥልጣን በሚፈቅደው መሠረት የሚጠበቅና የኤክሳይዝ ታክስ ያልተከፈለበት ዕቃ የሚቀመጥበት ቤት ወይም ሥፍራ ነው፡፡

፯/ "የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት/የተጣለበት ዕቃ" ማለት ከዚህ አዋጅ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ፩ ክፍል ፩ የተዘረዘሩ ዕቃዎች ናቸው፡፡

፰/ "የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት/የተጣለበት አገልግሎት" ማለት ከዚህ አዋጅ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ፩ ክፍል ፪ የተዘረዘሩት አገልግሎቶች ናቸው፡፡

፱/ "የኤክሳይዝ ታክስ ወይም ታክስ" ማለት በዚህ አዋጅ የተጣለው ታክስ ነው፡፡

፲/ "ከታክሱ ነፃ የሆኑ ዕቃዎች" ማለት ከዚህ አዋጅ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ፪ የተመለከቱ ዕቃዎች ናቸው፡፡

፲፩/ "ወደ ውጭ አገር መላክ" ማለት አንድን ዕቃ ከኢትዮጵያ ወደ ውጭ አገር ወይም የኤክስፖርት ምርቶች ወደሚመረቱበት ዞን መላክ ነው፡፡

## CHAPTER ONE

## GENERAL

### 1. Short title

This Proclamation may be cited as "the Excise Tax Proclamation No. 1186/2020."

### 2. Definitions

Unless the context otherwise requires, in this Proclamation:

1/ "Aircraft" means every description of conveyance by air of human beings or goods.

2/ "Arm's Length Transaction" means a transaction between persons dealing with each other at Fair, Market Value.

3/ "Denature" means to render unfit for human consumption for drink.

4/ "Distillery" means a licensed distiller's factory.

5/ "Customs Duty" means customs duty, surtax or any other similar tax imposed on the importation of goods.

6/ "Bonded Warehouse" means the building or place destined for storage of specified goods before the tax is paid and secured in accordance with the requirements of the Tax Authority.

7/ "Excisable Goods" means the goods specified in Part I of the First Schedule.

8/ "Excisable Services" means the services specified in Part II of the First Schedule.

9/ "Excise Tax or Tax" means the excise tax imposed under this Proclamation.

10/ "Exempt Goods" means goods specified in the Second Schedule.

11/ "Export" means to take or cause to be taken from Ethiopia to a foreign country, or to an export processing zone.

www.chilot.me

፲፪/ "የኤክስፖርት ምርቶች የሚመረቱበት ዞን" ማለት ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ ምርቶች የሚመረቱበት በኢንቬስትመንት ቦርድ የሚሰየም ዞን ነው፡፡

፲፫/ "ፋብሪካ" ማለት ፈቃድ የተሰጠው አምራች የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸውን ዕቃዎች የሚያመርትበት ወይም የሚያከማችበት ሥፍራ ሲሆን፣ ኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸው ዕቃዎች ለተጠቃሚው ኅብረተሰብ ለገበያ የሚቀርቡበትን ማናቸውንም የአምራቹን የሥራ ቦታ አይጨምርም፡፡

፲፬/ "ወደአገር ውስጥ ማስገባት" ማለት ዕቃዎችን ከውጭ አገር እና የኤክስፖርት ምርቶች ከሚመረቱበት ዞን ወደ ኢትዮጵያ ማስገባት ወይም እንዲገቡ ማድረግ ነው፡፡

፲፭/ "አስመጪ" ማለት ማናቸውም ወደአገር ውስጥ የሚገቡ ዕቃዎች ባለቤት የሆነ ሰው ወይም ዕቃዎቹ በይዞታው ሥር የሚገኝ ሰው ወይም በዕቃዎቹ ላይ ጥቅም ያለው ሰው ነው፡፡

፲፮/ "የኤክሳይዝ ቴምብር" ማለት የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት ዕቃ የኤክሳይዝ ታክስ የተከፈለበት መሆኑን ለማረጋገጥ የሚለጠፍ ምልክት ነው፡፡

፲፯/ "ዓለም አቀፍ ትራፊክ" ማለት አውሮፕላንን በሚመለከት በኢትዮጵያ ውስጥ ከአንድ ቦታ ወደሌላ ቦታ የሚደረገውን በረራ ሳይጨምር አውሮፕላኑን ለአየር በረራ ጥቅም ላይ ማዋል ነው፡፡

፲፰/ "ፈቃድ" ማለት የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸውን አገልግሎቶች በሚመለከት የምዝገባ የምስክር ወረቀት ሲሆን፣ የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸውን ዕቃዎች በሚመለከት እነዚህን ዕቃዎች ለማምረት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፯ መሠረት የሚሰጥ ፈቃድ ነው፡፡

፲፱/ "ፈቃድ የተሰጠው የአልኮል አምራች" ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፯ መሠረት ፈቃድ የተሰጠው አልኮል የሚያመርት ሰው ነው፡፡

፳/ "የተፈቀደለት አምራች" ማለት የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸውን ዕቃዎች የሚያመርት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፯ መሠረት ፈቃድ የተሰጠው ሰው ነው፡፡

፳፩/ "ማምረት" ማለት፦

ሀ) የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸውን ዕቃዎች ማምረት፣

12/ "Export Processing Zone" means a zone designated as such by the Management Board of the Ethiopian Investment Commission.

13/ "Factory" means any premises at which a licensed manufacturer is licensed to manufacture and store excisable goods, but does not include any part of the premises through which excisable goods are sold to the public.

14/ "Import" means to bring or cause goods to be brought into Ethiopia from a foreign country, a special economic zone or an export processing zone.

15/ "Importer" in relation to goods, means the person who owns the goods, or any other person who is, for the time being, in possession of or beneficially interested in the goods at the time of importation.

16/ "Excise Stamp" means a mark or an object affixed on excisable goods to indicate that Excise Tax has been paid on such goods;

17/ "International Traffic", in relation to an aircraft means any operation of the aircraft except as between two places in Ethiopia.

18/ "License" means in case of excisable services, the certificate of registration or in case of excisable goods, the license, issued under Article 17 of this Proclamation.

19/ "Licensed Distiller" means a distiller licensed under Article 17 of this Proclamation.

20/ "Licensed Manufacturer" means a person licensed under Article 17 of this Proclamation to manufacture excisable goods.

21/ "Manufacture" includes:

a) the production of excisable goods;

www.chilot.me

ለ) የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸውን ዕቃዎች በማምረት ሂደት ማናቸውንም ግብአት ወይም በከፊል የተጠናቀቀ ምርት ማምረት፣ ወይም

ሐ) አልኮልን ማጣራት፣ ማሻሻል፣ ለሚፈለገው አገልግሎት ማዘጋጀት፣ ለሰው አገልግሎት እንዳይውል ማድረግን ይጨምራል፡፡

፳፪/ "ማሻሻል" ማለት የአልኮል መጠጦችን ከሚያመርት ፋብሪካ የአልኮል መጠጥን በመረከብ እንደገና ማጣራት ወይም ልዩ ጣዕም እንዲታከልበት ማድረግ ነው፡፡

፳፫/ "የአልኮል መጠጥ" ማለት ማንኛውም የአልኮል ይዘቱ ከዜሮ ነጥብ አምስት በመቶ (ከዜሮ ነጥብ ፭ በመቶ) በላይ የሆነ የመጠጥ ዓይነት ነው፡፡

፳፬/ "የአልኮል ማጣሪያ መሣሪያ" ማለት ከኢትዮጵያ ባህላዊ ዕቃዎች ውጭ አልኮልን ለማምረት የሚያገለግል መሣሪያ ሲሆን፣ የዚህን መሣሪያ አካላት ይጨምራል፡፡

፳፭/ "ለአውሮፕላን መንገደኞች የሚውል ዕቃ" ማለት በአውሮፕላን የሚጓዙ መንገደኞች እንዲጠቀሙበት ወይም ለፍጆታ እንዲያውሉት በዓለም አቀፍ ትራፊክ ላይ የሚገኝ አውሮፕላን ውስጥ የተጫነ ዕቃ ሲሆን፣ በአውሮፕላን ውስጥ ለመንገደኞች የሚሸጥን ዕቃ ይጨምራል፡፡

፳፮/ "ወደአገር ውስጥ ገቡ የሚባልበት ጊዜ" የሚለው ሀገር በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፬ የተሰጠው ትርጉም ይኖረዋል፡፡

፳፯/ "የተጨማሪ እሴት ታክስ" ማለት በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር ፪፻፹፭/፲፱፻፺፬ የተጣለው ታክስ ነው፡፡

፳፰/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ሰው ነው፡፡

፳፱/ "የታክስ ባለሥልጣን" ማለት የገቢዎች ሚኒስቴር እንዲሁም የየክልሉ እና የከተማ አስተዳደሮች የገቢ ሰብሳቢ አካላት ናቸው፡፡

፴/ "ሚኒስቴር" እና "ሚኒስትር" ማለት እንደቅደም ተከተሉ የገንዘብ ሚኒስቴር እና የገንዘብ ሚኒስትር ነው፡፡

፴፩/ "አዋጅ" ማለት የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ነው፡፡

b) any intermediate or uncompleted process in the production of excisable goods; or

c) the distilling, rectifying, compounding, or denaturing of spirits.

22/ "Rectify" means to redistill spirits removed from a spirits receiver for the purpose of purifying or adding flavor.

23/ "Spirits" means any drink with zero point five percent (0.5%) or more alcohol volume.

24/ "Still" means a distilling apparatus and includes any part of a still.

25/ "Stores" means goods for use or consumption by passengers or crew on an aircraft or ship while in international traffic, and includes goods for sale on board such aircraft or vessel.

26/ "Time of Importation" has the meaning assigned to it under Article 4 of this Proclamation.

27/ "Value Added Tax" means the Value Added Tax Proclamation No. 285/2002.

28/ "Person" means a natural or juridical person.

29/ "Authority" means the Ministry of Revenue or Tax Authorities of the Regional Governments and City Administrations.

30/ "Minister" and "Ministry" means the Minister of Finance and the Ministry of Finance, respectively.

31/ 'Proclamation" means the Excise Tax Proclamation.

www.chilot.me

፴፪/ “የታክስ አስተዳደር አዋጅ” ማለት የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፱ሺ፹፫/፪ሺ፰ ነው፡፡

፴፫/ በታክስ አስተዳደር አዋጁ ለቃላትና ሐረጎች የተሰጠው ትርጉም በዚህ አዋጅ የተለየ ትርጉም ካልተሰጠው በስተቀር ለዚህ አዋጅም ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

፴፬/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትንም ፆታ ይጨምራል፡፡

## ፫. ትክክለኛ የገበያ ዋጋ

፩/ በአንድ የተወሰነ ጊዜ የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸው ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ትክክለኛ የገበያ ዋጋ ነው የሚባለው በዚያን ጊዜ ግንኙነት በሌላቸው ሰዎች መካከል በተካሄደ የጅምላ ግብይት ዕቃው ወይም አገልግሎቱ ሊያስገኝ ይችላል ተብሎ የሚጠበቀው ዋጋ ነው፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት በአንድ የተወሰነ ጊዜ የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸውን ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ትክክለኛ የገበያ ዋጋ ማወቅ ያልተቻለ እንደሆነ በፌደራል የታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀጽ ፫ ድንጋጌ መሠረት የዕቃው ወይም የአገልግሎቱ ትክክለኛ የገበያ ዋጋ ይወሰናል፡፡

## ፬. አገልግሎት ቀርቧል ወይም ዕቃዎች ወደአገር ውስጥ ገብተዋል የሚባልበት ጊዜ

፩/ የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸው ዕቃዎች ወደአገር ውስጥ ገቡ የሚባልበት ጊዜ ከሚከተሉት ሁኔታዎች አንዱ ሊሆን ይችላል:-

ሀ) ለአገር ውስጥ ፍጆታ የሚውሉ የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸው ዕቃዎች ከጉምሩክ ወደቦች ሲወጡ፣ ወደአገር ውስጥ የደረቅ ወደቦች የሚጓጓዙ እና የጉምሩክ ፎርማሊቲን በደረቅ ወደብ የሚያጠናቅቁ ዕቃዎች የጉምሩክ ፎርማሊቲ በሚከናወንበት ጊዜ፤

ለ) ወደአገር ውስጥ ከገቡ በኋላ ወደተፈቀደለት የጉምሩክ መጋዘን የሚጓጓዙ የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸው ዕቃዎች ለአገር ውስጥ ፍጆታ እንዲውሉ በተፈቀደለት የጉምሩክ መጋዘን የጉምሩክ ፎርማሊቲን ሲያጠናቅቁ፤

ሐ) የኤክስፖርት ምርቶች ከሚመረቱበት ዞን የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ለአገር ውስጥ ፍጆታ እንዲውሉ በሚወጡበት ጊዜ፤

32/ ‘Tax Administration Proclamation” means Tax Administration Proclamation No. 983/2016.

33/ Unless defined otherwise in this Proclamation the terms and phrases defined in the Tax Administration Proclamation shall also apply to this Proclamation.

34/ any expression in the masculine geneder includes the feminine.

## 3. Fair Market Value

1/ The fair market value of excisable goods or services at a particular time is the price that the goods or services would reasonably be expected to fetch in an arm's length transaction at that time at the wholesale level.

2/ If the open market value of excisable goods or services at a particular time cannot be determined under sub article 1 of this Article, the fair market value shall be the price which is an objective approximation of the price of the goods or services according to Article 3 of the Tax Administration Proclamation.

## 4. Time of Supply or Importation

1/ The time of importation of excisable goods may be one of the following:

a) for excisable goods cleared for home use directly at the port of importation or goods entered for removal to an inland station and there cleared for home use, at the time of customs clearance;

b) for excisable goods removed to a licensed warehouse subsequent to importation, at the time of final clearance from the warehouse for home use;

c) for excisable goods removed from an export processing zone or special economic zone for home use, at the time of removal for home use;

www.chilot.me

መ) በሌላ ማናቸውም ሁኔታ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ወደኢትዮጵያ ሲገቡ፣

፪/ የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለበት የአገልግሎት አቅርቦት ተከናወነ የሚባለው ከሚከተሉት በቀደመው ጊዜ ነው:-

ሀ) አገልግሎቱ በተሰጠበት ቀን፤

ለ) ለአገልግሎቱ የክፍያ መጠየቂያ ኢንቮይስ በተዘጋጀበት ቀን፤

ሐ) የአገልግሎቱ ክፍያ በሙሉ ወይም በከፊል በተከፈለበት ቀን፡፡

## ምዕራፍ ሁለት
## የኤክሳይዝ ታክስ የመክፈል ግዴታ

### ፭. የኤክሳይዝ ታክስ ስለመጣል

፩/ በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት የኤክሳይዝ ታክስ ተብሎ የሚታወቅ ታክስ በሚከተሉት ላይ ተጥሏል:-

ሀ) በተፈቀደለት አምራች በኢትዮጵያ ውስጥ የሚመረቱ የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸው ዕቃዎች፤

ለ) ወደኢትዮጵያ የሚገቡ የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸው ዕቃዎች፤

ሐ) በተፈቀደለት አገልግሎት ሰጪ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚሰጡ የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸው አገልግሎቶች፡፡

፪/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፱ በተደነገገው መሠረት ከአዋጁ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ፩ የተዘረዘሩት ኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች በሠንጠረዡ በተመለከተው የማስከፈያ ልክ የኤክሳይዝ ታክስ ይከፈልባቸዋል፡፡

### ፮. የኤክሳይዝ ታክስ የመክፈል ግዴታ

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት በዚህ አዋጅ የተጣለውን የኤክሳይዝ ታክስ የመክፈል ግዴታ አለባቸው:-

፩/ በኢትዮጵያ በሚመረቱ ዕቃዎች ላይ የተጣለውን የኤክሳይዝ ታክስ የተፈቀደለት አምራች፤

፪/ ወደኢትዮጵያ በሚገቡ ዕቃዎች ላይ የተጣለውን የኤክሳይዝ ታክስ አስመጪው፤

d) in any other case, at the time the excisable goods are brought into Ethiopia.

2/ The time of supply of excisable services shall be the earlier of:

a) the date on which the services are performed;

b) the date on which the invoice for the supply of the services is issued; or

c) the date on which payment for the supply of the services is received, in whole or part.

## CHAPTER TWO
## LIABILITY FOR EXCISE TAX

### 5. Imposition of Excise Tax

1/ Subject to this Proclamation, a tax, to be known as excise tax, shall be charged in accordance with the provisions of this Proclamation on:

a) excisable goods manufactured in Ethiopia by a licensed manufacturer;

b) excisable goods imported into Ethiopia;

c) excisable services supplied in Ethiopia by a licensed person.

2/ Excise tax shall be charged at the rate specified in the First Schedule for the excisable goods or services in force at the time the liability arises for excise tax as determined under Article 9 of this Proclamation.

### 6. Obligation to Pay Excise Tax

The following Shall pay the excise tax imposed under this Proclamation:

1/ on excise tax imposed on goods manufactured in Ethiopia the licensed manufacturer;

2/ on goods imported into Ethiopia the Importer of the excisable goods;

www.chilot.me

፫/ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚሰጡ አገልግሎቶች ላይ የተጣለውን የኤክሳይዝ ታክስ አገልግሎቱን ለመስጠት የተመዘገበው ሰው፡፡

**፯. <u>የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት ጊዜ</u>**

፩/ የተፈቀደለት አምራች በኢትዮጵያ ውስጥ በሚያመርታቸው የኤክሳይዝ ታክስ በሚከፈልባቸው ዕቃዎች ላይ የተመረቱት ዕቃዎች ከአምራቹ ፋብሪካ በሚወጡበት ጊዜ የኤክሳይዝ ታክሱን የመክፈል ግዴታ ይቋቋማል፡፡

፪/ ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም በተፈቀደለት አምራች ፋብሪካ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ ዕቃዎች ጥቅም ላይ በዋሉበት ጊዜ ከፋብሪካው እንደወጡ ይቆጠራል፡፡

፫/ የኤክሳይዝ ታክስ በተጣለባቸው አገልግሎቶች ላይ የተፈቀደለት ሰው የሚኖርበት የኤክሳይዝ ታክስ የመክፈል ግዴታ አገልግሎቱ በተሰጠበት ጊዜ ይቋቋማል፡፡

፬/ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ወደአገር ውስጥ የሚያስገባ አስመጪ በሚከተለው ጊዜ የኤክሳይዝ ታክሱን የመክፈል ግዴታ አለበት:-

ሀ) ሚኒስትሩ በሚያወጣው መመሪያ በልዩ ሁኔታ ካልፈቀደ በስተቀር የነዳጅ ምርቶች ወደአገር ውስጥ በሚገቡበት ጊዜ፣

ለ) በሌላ በማናቸውም ወደአገር ውስጥ በሚገባ ዕቃ ላይ የተጣለውን የኤክሳይዝ ታክስ፣ ዕቃው ወደአገር ውስጥ ሲገባ፡፡

፭/ የተፈቀደለት አምራች በዚህ አንቀጽ መሠረት ሊከፍል የሚገባውን የኤክሳይዝ ታክስ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፯ በተዘረዘረው አኳኋን መክፈል አለበት፣

፮/ የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸውን ዕቃዎች ወደአገር ውስጥ የሚያስገባ አስመጪ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፯ መሠረት ሊከፍል የሚገባውን የኤክሳይዝ ታክስ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፮ በተዘረዘረው አኳኋን መክፈል አለበት፡፡

**፰. <u>ከኤክሳይዝ ታክስ ነፃ የተደረጉ ዕቃዎች እና አገልግሎቶች</u>**

፩/ በዚህ አዋጅ ሌሎች አንቀጾች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የሚከተሉት ከኤክሳይዝ ታክስ ነፃ ተደርገዋል፡፡

3/ on services supplied in Ethiopia by the registered person.

**7. <u>Timing of Liability for Excise Tax</u>**

1/ The liability of a licensed manufacturer for excise tax on excisable goods manufactured in Ethiopia shall arise at the time of removal of the goods from the manufacturer's factory.

2/ For the purposes of this Proclamation, excisable goods that are consumed in a licensed manufacturer's factory shall be treated as removed from the factory at the time of consumption.

3/ The liability of a licensed person for excise tax on excisable services shall arise at the time of the supply of the services.

4/ The liability of an importer for excise tax on excisable goods imported into Ethiopia shall arise:

a) for petroleum products, at the time of importation unless under a directive to be issued by the Minister special permits are granted;

b) for any other excisable goods, at the time of importation.

5/ A licensed person shall pay the liability for excise tax arising under this Article, in accordance with Article 37 of this Proclamation;

6/ An importer shall discharge the liability for excise tax referred to in Article 6 of this Proclamation in accordance with Article 36 of this Proclamation.

**8. <u>Goods and Services Not Liable to Excise Tax</u>**

1/ Without Prejudice to the Provision of other Articles of this Proclamation no excise tax shall be charged on the following:

www.chilot.me

ሀ) ከዚህ አዋጅ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ፪ የተመለከቱትን ሁኔታዎች የሚያሟሉ ዕቃዎች፤

ለ) የተፈቀደለት የዕቃ መጋዘንን ጨምሮ በባለሥልጣኑ ቁጥጥር ሥር ሆነው ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ ዕቃዎች፤

ሐ) ከኢትዮጵያ ውጭ የተሰጡ አገልግሎቶች፤

መ) ከታክሱ ባለሥልጣን አስቀድሞ በተሰጠ የጽሑፍ ፈቃድ መሠረት የታክሱ ባለሥልጣን ሠራተኞች በተገኙበት ከተመረቱበት ፋብሪካ ከመውጣታቸው በፊት በአምራቹ ከጥቅም ውጭ እንዲሆኑ የተደረጉ የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸው ዕቃዎች፤

ሠ) ከኤክሳይዝ ታክስ ነፃ የመሆን መብት ላላቸው አካላት የሚሸጡ ኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸው ዕቃዎች እና አገልግሎቶች፤

ረ) ለኢኮኖሚ፣ ለማህበራዊና ለአስተዳደራዊ ምክንያቶች በሚኒስትሩ ከኤክሳይዝ ታክስ ነፃ የተደረጉ ዕቃዎች፤

ሰ) ለሕክምና አገልግሎት እንዲውል ለሰው በመጠጥነት አገልግሎት ሊሰጥ በማይችልበት አኳኋን የተመረተ አልኮል፤

ሸ) በሚከተለው ሁኔታ በአደጋ ወይም በሌላ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት የጠፉ ወይም የተበላሹ የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸው ዕቃዎች፡-

(፩) ዕቃዎች የመጫን ወይም የማውረድ ተግባርን ጨምሮ ዕቃዎቹ ከአምራቹ ፋብሪካ በመውጣት ላይ ባሉበት ጊዜ፤

(፪) ከፋብሪካው ከመውጣታቸው በፊት ዕቃዎቹ በተመረቱበት በአምራቹ ፋብሪካ ውስጥ ባሉበት ጊዜ፤

(፫) ዕቃዎቹ ኢትዮጵያ ከመድረሳቸው በፊት በአውሮፕላን ወይም በመርከብ በመጓጓዝ ላይ ባሉበት ጊዜ፡፡

፪/ የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸው አገልግሎቶች ከኢትዮጵያ ውጭ የተሰጡ ናቸው የሚባለው አገልግሎቶቹ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኝ የንግድ ሥራ ቦታ የተሰጡ ሆነው ጥቅም ላይ የሚውሉት ግን ከኢትዮጵያ ወጪ ሲሆኑ ነው፡፡

a) exempt goods which meet the conditions set out in the Second Schedule;

b) excisable goods exported under customs control, including those stored in the approved warehouse;

c) excisable services exported from Ethiopia;

d) excisable goods that the manufacturer has destroyed, with the prior written permission of the Authority, under the supervision of the officer's of the Authority prior to their removal from the factory in which they were manufactured;

e) excisable goods and services that are supplied to entities that are exempt from excise tax by law;

f) goods and services exempted from excise tax by the Minister due to economic, social and administrative reasons;

g) denatured alcohol produced in a manner that it cannot be used for human consumption;

h) excisable goods that have been lost or destroyed by accident or other unavoidable cause:

(1) in the course of removal of the goods by the manufacturer from the manufacturer's factory including when loading or unloading the goods;

(2) in the factory of the manufacturer in which the goods were manufactured before removal from the factory;

(3) on board an aircraft or vessel prior to importation into Ethiopia.

2/ Excisable services shall be considered to be exported from Ethiopia if the services are supplied from a place of business in Ethiopia for use or consumption outside Ethiopia.

www.chilot.me

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተፈፃሚ የሚሆነው የታክሱ ባለሥልጣን አገልግሎቶቹ በኢትዮጵያ ውስጥ ጥቅም ላይ ያልዋሉ መሆኑን ሲያምንበት ነው፡፡

፬/ የተፈቀደለት አምራች በአደጋ ወይም በሌላ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ለጠፉ ወይም ለተበላሹ ዕቃዎች ካሣ ያገኘ እንደሆነ እና ካሣው የኤክሳይዝ ታክሱን የሚጨምር ከሆነ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) (መ) ተጠቃሚ ሊሆን አይችልም፡፡

**፱. <u>የኤክሳይዝ ታክስ ስሌት መሠረት</u>**

፩/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌ ተፈፃሚ የሚሆነው ከአዋጁ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ፩ የተጣለው የኤክሳይዝ ታክስ ማስከፈያ መሠረት የዕቃዎቹ ወይም የአገልግሎቶቹ የኤክሳይዝ ታክስ ማስከፈያ ዋጋ በሚሆንበት ጊዜ ነው፡፡

፪/ ወደኢትዮጵያ የሚገቡ ዕቃዎች የኤክሳይዝ ታክስ ማስከፈያ ዋጋ የሚከተሉት ድምር ይሆናል:-

ሀ) በዕቃው ላይ የጉምሩክ ቀረጥ የሚከፈል ቢሆንም ባይሆንም በጉምሩክ አዋጅ መሠረት የሚሠላው የዕቃው ዋጋ፤

ለ) በጉምሩክ አዋጅ መሠረት ሊከፈል የሚገባው የጉምሩክ ቀረጥ፡፡

፫/ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚመረቱ የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸው ዕቃዎች የኤክሳይዝ ታክስ ማስከፈያ ዋጋ የፋብሪካ መሸጫ ዋጋ ሲሆን፣ የሚከተሉትን አይጨምርም:-

ሀ) በዕቃ አቅርቦት ላይ የተጣለውን የተጨማሪ እሴት ታክስ፤

ለ) የኤክሳይዝ ቴምብር (ካለ) ወጪ፤ እና

ሐ) የተመላሽ ዕቃ መያዣዎችን ወጪ፤

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፭) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው አገልግሎቶች ዋጋ የሚከተለው ይሆናል:-

ሀ) የተመዘገበው ሰው የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን አገልግሎቶች የሸጠው ግንኙነት በሌላቸው ሰዎች መካከል በተደረገ ግብይት ከሆነ ተከፋይ የሆነው የአገልግሎቱ ዋጋ፣ ኮሚሽን ወይም ሌላ ክፍያ፤

3/ Sub-Article (2) of this Article shall apply only if the Authority is satisfied that the services have not been consumed in Ethiopia.

4/ Sub-Article (1) (d) shall not apply if the licensed manufacturer has been compensated for the loss of the excisable goods and the compensation includes the excise tax payable on the goods.

**9. <u>Excisable Value</u>**

1/ This Article shall apply where the First Schedule specifies a rate of excise tax payable by reference to the excisable value of excisable goods or services.

2/ The excisable value of excisable goods imported into Ethiopia shall be the sum total of the following amounts:

a) the customs value of the goods as determined under the Customs Proclamation, whether or not any Customs Duty is payable on the goods;

b) the amount of Customs Duty (if any) payable on the goods under the Customs Proclamation.

3/ The excisable value of excisable goods manufactured in Ethiopia shall be the ex-factory selling price of the goods, but not including the following:

a) the value added tax payable on the supply of the goods;

b) the cost of excise stamps, if any; and

c) the cost of returnable containers.

4/ without Prejudice to the provision of Sub-Article (5) of this Article, the excisable value of excisable services shall be:

a) if the excisable services are supplied by a registered person in an arm's length transaction, the fee, commission or charge payable for the services;

www.chilot.me

ለ) በሌላ ማናቸውም ሁኔታ የአገልግሎቱ ትክክለኛ የገበያ ዋጋ፡፡

፭/ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው አገልግሎቶች ዋጋ በአገልግሎቱ ላይ የሚከፈለውን የተጨማሪ እሴት ታክስ አይጨምርም፣

## ፲. ማስተካከያ ስለማድረግ

፩/ ሚኒስትሩ በሚያወጣው መመሪያ ከዚህ አዋጅ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ፩ በተመለከተው የማስከፈያ ምጣኔ ላይ ከ፲ በመቶ ያልበለጠ ምጣኔ ሊጨምር ወይም ሊቀንስ ይችላል፡፡

፪/ የታክስ ባለሥልጣኑ ከዚህ አዋጅ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ፩ በቁርጥ በተጣለው የኤክሳይዝ ታክስ ማስከፈያ መጣኔ ላይ ሚኒስትሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ የዋጋ ንረት ማስተካከያ ማድረግ አለበት፡፡

## ፲፩. የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸው ዕቃዎች የፋብሪካ መሸጫ ዋጋ

፩/ የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸው ዕቃዎች የፋብሪካ መሸጫ ዋጋ ነው የሚባለው:-

ሀ) አምራቹ የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸውን ዕቃዎች የሸጠው ግንኙነት በሌላቸው ሰዎች መካከል በሚደረግ ግብይት ለገዥው የሆነ እንደሆነ፣ ገዥው የከፈለው ዋጋ፤

ለ) በሌላ በማናቸውም ሁኔታ ዕቃው ከአምራቹ ፋብሪካ በወጣበት ጊዜ ያለው ትክክለኛ የገበያ ዋጋ፡፡

፪/ በፋብሪካ መሸጫ ዋጋ ላይ የተከፈለው የኤክሳይዝ ታክስ በግብይቱ ደረሰኝ ላይ ተለይቶ መታየት አለበት፡፡

## ፲፪. የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸው ዕቃዎች መጠን

፩/ ይህ አንቀጽ ተፈፃሚ የሚሆነው ከአዋጁ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ፩ መሠረት በዕቃዎቹ ላይ የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለው የዕቃዎቹን ብዛት ወይም ክብደት መሠረት ባደረገ መጠን በሚሆንበት ጊዜ ነው፡፡

፪/ በሚከተሉት ሁኔታዎች የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች የኤክሳይዝ ታክስ ማስከፈያ መጠን የሚወሰነው ከዕቃው ጋር የሚሸጠውን የዕቃውን ማሸጊያ እና በውስጡ የያዘውን ክብደት መሠረት በማድረግ ይሆናል:-

b) in any other case, the fair market value of the services.

5/ The excisable value of excisable services shall not include the value added tax, if any, payable on the supply of the services.

## 10. Adjustment for Inflation

1/ The Minister by a directive to be issued it may increase or decrease not exceeding 10% in the rate changed it first schedule in relation to this proclamation.

2/ The Authority shall, in accordance with the directive issued by the Minister, adjust the specific rate of excise tax specified in first schedule of this Proclamation at least once a year to take inflation into account.

## 11. Ex-factory Selling Price of Excisable Goods

1/ The ex-factory selling price of excisable goods shall be:

a) if the excisable goods are sold by the manufacturer, other than to a purchaser in an arm's length transaction, the price payable by the purchaser;

b) in any other case, the open market value of the goods at the time of removal from the manufacturer's factory.

2/ The Excise tax paid on the ex-factory selling price shall be separately shown in the invoice.

## 12. Quantity of Excisable Goods

1/ This Article shall apply where the First Schedule specifies a rate of excise tax payable by reference to a quantity measured by volume or weight.

2/ If:

www.chilot.me

ሀ) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ወደኢትዮጵያ በሚገቡበት ወይም በተፈቀደለት አምራች ከተመረቱበት ፋብሪካ በሚወጡበት ጊዜ ከዕቃው ጋር አብሮ ከሚሸጥ ማሸጊያ ጋር ወይም የዚህ ዓይነት ዕቃዎች በችርቻሮ በሚሸጡበት አብዛኛውን ጊዜ አብረው ከሚሸጡ ማሸጊያዎች ጋር ሲሆን፣ እና

ለ) ማሸጊያው:-

(፩) የተጣራ ክብደቱ ያልተፃፈበት ከሆነ፣ ወይም

(፪) በሚሸጥበት ጊዜ በውስጡ ያለው ይዘት በተለምዶ የሚታወቅ ባለመሆኑ ወይም አብዛኛውን ጊዜ ይዘቱ የሚታወቅ ባለመሆኑ ትክክለኛ ብዛቱን ወይም ክብደቱን ማወቅ የማይቻል ከሆነ፡፡

ሐ) የዕቃው ባለቤት የማሸጊያውን የተጣራ ክብደት ትክክለኛነት የታክስ ባለሥልጣኑን በሚያረካ አኳኋን ማስረዳት ካልቻለ፣ የኤክሳይዝ ታክስ በተጣለባቸው ዕቃዎች ላይ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈለው በማሸጊያው እና በውስጡ በያዘው ዕቃ ጠቅላላ ክብደት ላይ ይሆናል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በሚከተሉት ሁኔታዎች በማሸጊያው ላይ ከተገለፀው መጠን ያላነሰ ዕቃ በውስጡ እንዳለው ይቆጠራል:-

ሀ) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ወደኢትዮጵያ በሚገቡበት ወይም በተፈቀደለት አምራች ከተመረቱበት ፋብሪካ በሚወጡበት ጊዜ ከዕቃው ጋር አብሮ ከሚሸጥ ማሸጊያ ጋር ወይም የዚህ ዓይነት ዕቃዎች በችርቻሮ በሚሸጡበት አብዛኛውን ጊዜ አብረው ከሚሸጡ ማሸጊያዎች ጋር ሲሆን፣ እና

ለ) ማሸጊያው:-

(፩) የሚይዘው የተወሰነ ብዛት ያለው ዕቃ በማሸጊያው ላይ የተፃፈበት ከሆነ፣ ወይም

(፪) በሚሸጥበት ጊዜ በውስጡ ያለው ይዘት በተለምዶ የሚታወቅ ከሆነ፡፡

a) excisable goods are imported into Ethiopia, or removed from the factory of a licensed manufacturer, in a package intended for sale with, or of a kind usually sold with the goods in a sale by retail; and

b) the package:

(1) is not marked or labeled with a net weight; or

(2) is not commonly sold as containing, or is not commonly reputed to contain, a specific quantity or weight.

c) the owner of the goods is unable to satisfy the Authority of the correct net weight of the package, the excisable goods shall be liable to excise tax according to the gross weight of the package and its contents.

3/ without prejudice to the provision of sub-article (4) of this Article, if:

a) excisable goods are imported into Ethiopia, or removed from the factory of a licensed manufacturer, in a package intended for sale with, or of a kind usually sold with, the goods in a sale by retail; and

b) the package:

(1) is marked, or labeled as containing a specific quantity of the goods; or

(2) is commonly sold as containing, or is commonly reputed to contain, a specific quantity of the goods,

the package shall be treated as containing not less than the specific quantity.

www.chilot.me

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) የተመለከተው ማሸጊያ የያዘው መጠን ከተወሰነው መጠን በላይ የሆነ እንደሆነ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈለው በትክክለኛው መጠን ላይ ይሆናል፡፡

፭/ የታክሱ ባለሥልጣን በማምረት ሂደት ለሚያጋጥም ቁርጥራጭ እና ውዳቂ የሚፈቀደውን መጠን እና የሚፈቀድበትን ሁኔታ በመመሪያ ይወስናል፡፡

**፲፫. <u>የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸው አገልግሎቶች የተሰጡበት ቦታ</u>**

የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸው አገልግሎቶች የተሰጡት አገልግሎት ሰጪው ኢትዮጵያ ውስጥ ባለው የንግድ ሥራ ቦታ ከሆነ አገልግሎቱ ኢትዮጵያ ውስጥ እንደተሰጠ ይቆጠራል፡፡

**፲፬. <u>በጥሬ ዕቃ/ግብዓት ላይ የተከፈለን ታክስ ስለማቀናነስ</u>**

፩/ የተፈቀደለት አምራች የኤክሳይዝ ታክስ በሚከፈልባቸው ወደ አገር ውስጥ በገቡ ወይም በአገር ውስጥ በተመረቱ ጥሬ ዕቃዎች/ግብዓቶች ላይ የኤክሳይዝ ታክስ የከፈለ እንደሆነ እና እነዚህን ጥሬ ዕቃዎች/ግብዓቶች የመጨረሻውን ምርት (ከዚህ በኋላ "የመጨረሻ ምርት") ለማምረት በግብዓትነት የተጠቀመባቸው ከሆነ፣ በጥሬ ዕቃዎቹ/ግብዓቶቹ ላይ የተከፈለው ታክስ በመጨረሻ ምርቶቹ ላይ ከሚከፈለው የኤክሳይዝ ታክስ ጋር እንዲቀናነስ ይደረጋል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው አልኮልን፣ ትንባሆን እና ስኳርን አይጨምርም፡፡

**<u>ምዕራፍ ሦስት</u>**
**<u>ስለፈቃድ</u>**
**<u>ክፍል አንድ</u>**

**<u>ፈቃድ ለማግኘት ስለሚቀርብ ማመልከቻ</u>**

**፲፭. <u>ፈቃድ ማግኘት የሚያስፈልጋቸው ሥራዎች</u>**

፩/ ማንኛውም ሰው ከታክስ ባለሥልጣኑ ፈቃድ ካላገኘ ወይም በታክስ ባለሥልጣኑ ዘንድ ካልተመዘገበ በስተቀር በሚከተሉት ሥራዎች ላይ መሠማራት አይችልም:-

ሀ) በኢትዮጵያ ውስጥ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ማምረት፣

4/ If the package referred to in Sub-Article (3) of this Article contains more than the specific quantity, excise tax shall be computed on the actual quantity.

5/ The Authority may by directive determine and specify the allowance for tare or wastage that may be granted and the conditions under which it is granted.

**13. <u>Place of Supply of Excisable Services</u>**

A supply of excisable services shall be deemed to be made in Ethiopia if the services are supplied from a place of business of the supplier in Ethiopia.

**14. <u>Relief for Raw Materials</u>**

1/ Where excise tax has been paid in respect of excisable goods imported into, or manufactured in Ethiopia by a licensed manufacturer and which have been used as raw materials in the manufacture of other excisable goods (hereinafter referred to as "finished goods"), the excise tax paid on the raw materials shall be offset against the excise tax payable on the finished goods.

2/ The provisions of Sub-Article (1) of this Article shall not apply to alcohol, tobacco and sugar.

**<u>CHAPTER THREE</u>**

**<u>LICENSING</u>**

**<u>Part One</u>**
**<u>Application for a License</u>**

**15. <u>Activities Requiring a License</u>**

1/ A person shall not undertake any of the following activities unless the person is licensed or registered by the Authority to undertake the activity:

a) the manufacture of excisable goods in Ethiopia;

www.chilot.me

ለ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፱ በተደነገገው መሠረት፣ ሚኒስትሩ በሚያወጣው መመሪያ የኤክሳይዝ ቴምብር ሊለጠፍባቸው ይገባል የተባሉ የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸውን ዕቃዎች ማቅረብ፣

ሐ) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን አገልግሎቶች ማቅረብ፣

መ) ሚኒስትሩ በሚያወጣው መመሪያ ፈቃድ የማግኘት ግዴታ በሚጥልባቸው ሌሎች ሥራ ዘርፎች መሠማራት፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገውን በመተላለፍ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች በማምረት ወይም አገልግሎቶችን በመስጠት ሥራ ላይ የተሠማራ ሰው ከዚህ አዋጅ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ፩ የተጣለውን የኤክሳይዝ ታክስ እንዲከፍል ይገደዳል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የኤክሳይዝ ታክስ እንዲከፍል የሚገደድ ሰው፡-

ሀ) በታክስ ባለሥልጣኑ በተጠየቀ ጊዜ ታክሱን ወዲያውኑ መክፈል አለበት፣

ለ) ከኤክሳይዝ ታክሱ በተጨማሪ በዚህ አዋጅ እንዲሁም በታክስ አስተዳደር አዋጅ በተደነገገው መሠረት በወንጀል ተጠያቂ ይሆናል እንዲሁም ቅጣትና ወለድ እንዲከፍል ይደረጋል፡፡

**፲፮. ለፈቃድ ማመልከቻ ስለማቅረብ**

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፭ (፩) በተዘረዘሩት የሥራ መስኮች ለመሠማራት የሚፈልግ ሰው በአንቀጽ ፲፭ (፩) ከተዘረዘሩት መካከል ለሚሠማራበት የሥራ መስክ ፈቃድ እንዲሰጠው ለታክስ ባለሥልጣኑ ማመልከቻ ማቅረብ አለበት፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚቀርብ ማመልከቻ፡-

ሀ) በተፈቀደው ቅጽ መሠረት ሊቀርብ፣

ለ) የፈቃድ ክፍያ ሊከፈልበት፣

ሐ) በባለሥልጣኑ በተወሰነው አኳኋን ሊቀርብ፣ ይገባል፡፡

b) the importation into Ethiopia of excisable goods specified by the Minister under Article 29 as requiring an excise stamp;

c) the supply of excisable services; or

d) the carrying out of any other activity in Ethiopia for which the Minister by a Directive, may impose a requirement or a license.

2/ A person who manufactures excisable goods or supplies excisable services in contravention of Sub-Article (1) of this Article shall be liable for the excise tax payable in respect of the excisable goods or services at the rate specified in the First Schedule.

3/ A person who is liable to pay the excise tax under Sub-Article (2) of this Article:

a) shall pay the tax immediately upon demand made by the Authority;

b) shall be in addition to any penalty and interest imposed on the person under this Proclamation or the Tax Administration Proclamation.

**16. Applications for a License**

1/ A person who intends to undertake any of the activities specified in Article 15(1) shall apply to the Authority for a license for any of the activities specified under Article 15 (1).

2/ An application under Sub-Article (1) of this Article shall be:

a) in the prescribed form;

b) accompanied by the prescribed fees;

c) lodged with the Authority in the prescribed manner.

www.chilot.me

## ክፍል ሁለት
## ፈቃድ ስለመስጠት

### ፲፯. ፈቃድ መስጠት

፩/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የታክስ ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፮ መሠረት የሚቀርብለትን ማመልከቻ በመመርመር ለአመልካቹ ፈቃዱን ሊሰጥ ወይም ሊከለክል ይችላል፡፡

፪/ የታክስ ባለሥልጣኑ ፈቃድ ሊከለክል የሚችለው የሚከተሉት ሁኔታዎች መኖራቸውን ሲያረጋግጥ ይሆናል:-

ሀ) አመልካቹ በዚህ አዋጅ ወይም በታክስ አስተዳደር አዋጅ መሠረት በታክስ መሰወር ወይም በታክስ ማጭበርበር ወንጀል ተከሶ የተፈረደበት ከሆነ፤

ለ) አመልካቹ በማናቸውም ሕግ እምነት በማጉደል ወይም በማጭበርበር ወንጀል ተከሶ የተፈረደበት ከሆነ፤

ሐ) አመልካቹ:-

(፩) የከሰረ ወይም ዕዳውን ለመክፈል ያልቻለ ከሆነ፣

(፪) በኪሣራ ምክንያት ሀብቱ በመጣራት ላይ ያለ ወይም ባለአደራ የተሰየመበት ከሆነ፣

መ) ማመልከቻው የቀረበው የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ምርቶች ለማምረት ከሆነ በማመልከቻው የተመለከተው ፋብሪካ፣ ማምረቻ፣ መሣሪያ ምርቱን ለማምረት ወይም የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ለመከታተል በቂ ካልሆነ፣

ሠ) አመልካቹ በማናቸውም የታክስ ሕግ በተደነገገው መሠረት ትክክለኛውን የሂሳብ መዝገብ ያልያዘ፣ ወይም በማናቸውም የታክስ ሕግ የተጣለበትን ግዴታ ያልተወጣ ወይም በታክስ ባለሥልጣኑ በተጠየቀው መሠረት በተወሰነ ጊዜ ውስጥ የሂሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታውን ለመወጣት ግዴታ ለመግባት ያልተስማማ፤

ረ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) (ሀ) (ለ) (ሐ) እና (ሠ) የተመለከተው ከአመልካቹ ጋር ግንኙነት ያለውን ሰው የሚመለከት ሲሆን፣ ይህ አንቀጽ ተፈፃሚ የሚሆነው የታክስ

## Part Two
## Issue of Licenses

### 17. Issue of License

1/ Without Prejudice to the provision of Sub-Article (2) of this Article, the Authority shall consider an application under Article 16 and may grant or refuse to issue the applicant with a license.

2/ The Authority may refuse an application under if satisfied that:

a) the applicant has been convicted of tax evasion or fraud under this Proclamation or the Tax Administration Proclamation;

b) the applicant has been convicted of an offence involving dishonesty or fraud under any law;

c) the applicant:

(1) is or has been declared bankrupt or insolvent;

(2) is in the process of liquidation or receivership;

d) in the case of an application to be a manufacturer of excisable goods, the factory, plant or equipment, specified in the application is not adequate to manufacture or secure excisable goods;

e) the applicant has not kept proper records as required under any tax law or has otherwise failed to comply with its obligations under a tax law; or if he does not agree to comply with his obligation to keep proper records within a given time frame as required by the Authority;

f) paragraphs (a), (b), (c) and (e) of Sub-Article (2) of this Article apply to a person related to the applicant and the Authority is satisfied that the related

www.chilot.me

ባለሥልጣኑ ከአመልካቹ ጋር ግንኙነት ያለው ሰው ፈቃድ በተጠየቀበት የሥራ መስክ ውስጥ የሚሠማራ ለመሆኑ በቂ ጥርጣሬ ያለው በሚሆንበት ጊዜ ነው፡፡

፫/ በዚህ አዋጅ መሠረት ከሚሰጠው ፈቃድ ጋር በተያያዘ የታክሱ ባለሥልጣን አስፈላጊ መስሎ ከታየው የውል ቃሎችና ሁኔታዎች ወይም ገደቦች እንዲኖሩ ሊያደርግ ይችላል፡፡

፬/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፮ መሠረት የፈቃድ ማመልከቻ ለሚያቀርብ ሰው የታክስ ባለሥልጣኑ በማመልከቻው መሠረት የተሰጠውን ውሳኔ ማመልከቻው ከቀረበበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር የ፴ ቀን ጊዜ ውስጥ በጽሁፍ መግለጽ አለበት፡፡ ማመልከቻው ውድቅ የተደረገ ከሆነ ውድቅ የተደረገበት ምክንያት መገለጽ አለበት፡፡

፭/ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚሰጠው ፈቃድ በታክስ ባለሥልጣኑ በተሰጠው ፈቃድ ላይ ከተመለከተው ቀን ጀምሮ የሚፀና ሲሆን፣ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፩ መሠረት ካልተሠረዘ በስተቀር ላልተወሰነ ጊዜ የፀና ይሆናል፡፡

## ፲፰. <u>የፈቃዱ ቅርጽ</u>

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፯ መሠረት የሚሰጠው ፈቃድ በፀደቀው ቅጽ መሠረት የሚሰጥ ይሆናል፡፡

፪/ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ለሚያመርት ሰው የሚሰጥ ፈቃድ የሚከተሉትን መያዝ አለበት:-

ሀ) አምራቹ እንዲያመርት የተፈቀደለትን የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበትን ዕቃ ምድብ ወይም ምድቦች፣

ለ) አምራቹ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ምርቶች እንዲያመርት የተፈቀደለትን ፋብሪካ/ፋብሪካዎች፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ መሠረት በተሰጠ ፈቃድ የተመለከተው ፋብሪካ ማምረት የሚችለው በፈቃዱ የተመለከተውን የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበትን ዕቃ ምድብ/ምድቦች ብቻ ነው፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ መሠረት በተሰጠ ፈቃድ በተመለከተው ፋብሪካ የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸውን ዕቃዎች ማምረት የሚችለው በፈቃዱ ላይ አምራች በሚል የተመለከተው ሰው ብቻ ነው፡፡

person is reasonably expected to be involved in the conduct of the activity to which the application relates.

3/ The Authority may impose such terms, conditions or restrictions as it considers appropriate in relation to a license issued under this Article.

4/ The Authority shall give an applicant for a license under Article 16 written notice of the decision on the application within 30 days from the date the application is submitted and if the application is refused, the notice shall include reasons for the refusal.

5/ A license shall take effect from the date specified therein by the Authority and shall unless earlier suspended, remain in force until cancelled under Article 21.

## 18. <u>Form of License</u>

1/ The license issued under Article 17 shall be in the prescribed form.

2/ A license issued to a manufacturer of excisable goods shall specify the following:

a) the class or classes of excisable goods that the manufacturer is licensed to manufacture;

b) the factory/factories at which the manufacturer is permitted to manufacture excisable goods.

3/ A factory specified in a license issued under this Article shall be used only for the manufacture of the class/classes of excisable goods specified in the license.

4/ Only the person specified as the licensed manufacturer in a license issued under this Article shall manufacture excisable goods in the factory specified in the license.

www.chilot.me

፭/ የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸውን አገልግሎቶች በማቅረብ ሥራ ላይ ለተሠማራ ሰው የሚሰጠው ፈቃድ የሚሰጠውን አገልግሎት የሚገልፅ መሆን አለበት፡፡

**፲፱. ፈቃድ የተሰጠው ሰው ግዴታዎች**

፩/ ፈቃድ የተሰጠው ሰው የሚከተሉትን የመፈፀም ግዴታ አለበት:-

ሀ) የተሰጠውን ፈቃድ ዋና ቅጂ የንግድ ሥራውን በሚያካሂድበት ዋና መሥሪያ በግልጽ በሚታይ ቦታ መለጠፍ፣

ለ) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን አገልግሎቶች በሚመለከት የፈቃዱን የተረጋገጠ ኮፒ የንግድ ሥራውን በሚያካሂድበት ቦታ ሁሉ የመለጠፍ፡፡

፪/ ፈቃድ የተሰጠው ሰው የሚከተሉትን መረጃዎች በሚመለከት ለታክስ ባለሥልጣኑ በጽሁፍ ማስታወቂያ የመላክ ግዴታ አለበት:-

ሀ) ፈቃድ የተሰጠበትን ሥራ ያቆመ እንደሆነ፣

ለ) የተፈቀደለት አምራች የሚያከናውነውን ዋና ተግባር መጠሪያ፣ አድራሻ፣ ሥራውን የሚያከናውንበትን ቦታ፣ ባለቤትነት፣ የመተዳደሪያ ደንብ ወይም የሥራውን ባህሪ የለወጠ እንደሆነ፣

ሐ) የተፈቀደለት አምራች የሥራውን እንቅስቃሴ ለተወሰነ ጊዜ በጊዜያዊነት ያቋረጠ እንደሆነ፣ ወይም

መ) የተፈቀደለትን አምራች በሚመለከት የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ለማምረት በሚጠቀምበት በፈቃዱ በተመለከተው ፋብሪካ ወይም ማምረቻ እና መሣሪያ ላይ ለውጥ የተደረገ እንደሆነ፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የሚላከው ማስታወቂያ ለታክሱ ባለሥልጣን በሚከተለው ጊዜ ውስጥ እንዲደርስ መደረግ አለበት:-

ሀ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) (ሐ) መሠረት የሚቀርበውን ማስታወቂያ በሚመለከት የንግድ ሥራው የተዘጋው ባልታቀደ ሁኔታ ከሆነ፣ የንግድ ሥራውን ለመዝጋት ምክንያት የሆነው ሁኔታ ካጋጠመበት ቀን ጀምሮ በ፯ ቀናት ውስጥ፣

5/ A license issued to a supplier of excisable services shall specify the excisable services offered.

**19. Obligations of Licensed Person**

1/ A licensed person has the obligation to carry out the following:

a) display in a conspicuous place the original of the license at the principal place of business;

b) in case of excisable services, a certified copy of the license at every other place of business.

2/ A licensed person shall notify the Authority, in writing:

a) if the licensed person ceases to carry on the activity for which the license is issued;

b) if there is any change in the name, address, place of business ownership, constitution, or nature of the principal activity or activities carried on by the licensed person;

c) of any period in which the licensed person closes operations on a temporary basis; or

d) if, the case of a licensed manufacturer, there is any change in the factory specified in the license, or the plant and equipment used to manufacture excisable goods.

3/ A notification under Sub-Article (2) shall be lodged with the Authority:

a) in the case of a notification under Sub-Article (2) (c) of this Article where the closure was unplanned, within 7 days after the event causing the closure;

www.chilot.me

ለ) በሌላ ማናቸውም ሁኔታ ማስታወቂያውን ለመላክ ምክንያት የሆነው ሁኔታ ባጋጠመ በ፯ ቀናት ውስጥ ለታክስ ባለሥልጣኑ እንዲደርስ መደረግ አለበት፡፡

## ክፍል ሦስት
## ፈቃድን ስለማገድና ስለመሠረዝ

### ፳. ፈቃድን ስለማገድ

፩/ የታክሱ ባለሥልጣን ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ በዚህ አዋጅ መሠረት የተሰጠውን ፈቃድ ማገድ ይችላል:-

ሀ) ፈቃድ ከተሰጠው ሰው የንግድ ሥራ ጋር በተያያዘ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፱ (፪) (ሀ)፣ (ለ)፣ ወይም (ሐ) የተዘረዘሩ ሁኔታዎች ያጋጠሙ እንደሆነ፤

ለ) ፈቃድ የተሰጠው ሰው በዚህ አዋጅ ወይም በታክስ አስተዳደር አዋጅ በተመለከተው መሠረት ተገቢውን የሂሳብ መዝገብ ያልያዘ ወይም ማናቸውንም በዚህ አዋጅ የተጣለበትን ግዴታ ያልተወጣ እንደሆነ፤

ሐ) ፈቃድ የተሰጠው ሰው በፈቃዱ የተመለከቱ ሁኔታዎችን የጣሰ እንደሆነ፤

መ) ፈቃድ የተሰጠው ሰው ለታክስ ባለሥልጣኑ የሀሰት ወይም አሳሳች መረጃን የሰጠ እንደሆነ፣

ሠ) የተፈቀደለትን አምራች በሚመለከት፣ በፈቃዱ የተመለከተው ፋብሪካ፣ ማምረቻ ወይም መሣሪያ ኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ምርቶች ለማምረት ከዚያን ጊዜ በኋላ አጥጋቢ ሆነው ያልተገኙ እንደሆነ፣

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የታክስ ባለሥልጣኑ ፈቃድን ያገደ እንደሆነ ፈቃድ ለተሰጠው ሰው ፈቃዱ የታገደ መሆኑን የሚገልጽ ማስታወቂያ በጽሁፍ መስጠት አለበት፡፡

፫/ ፈቃድን ለማገድ የተሰጠ ውሳኔ ተፈፃሚ የሚሆነው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት ማስታወቂያው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ነው፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት ፈቃዱ የታገደ መሆኑን የሚገልጽ ማስታወቂያ የደረሰው ሰው የዕግዱ ማስታወቂያ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በ፲፬ ቀናት ውስጥ ወይም የታክስ ባለሥልጣኑ በሚሰጠው ተጨማሪ ጊዜ ውስጥ ዕግዱን በመቃወም የይግባኝ ማመልከቻ ለባለሥልጣኑ የታክስ ቅሬታ አጣሪ የሥራ ክፍል በጽሁፍ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

b) in any other case, at least 7 days prior to the event requiring notification occurs to the Authority of Tax.

## Part Three
## Suspension and Cancellation of Licenses

### 20. Suspension of License

1/ The Authority may suspend a license issued under this Proclamation if the Authority is satisfied that:

a) any of the matters specified in Article 19 (2) (a), (b) or (c) apply to the licensed person;

b) the licensed person has not kept proper records as required under this Proclamation or the Tax Administration Proclamation, or has otherwise failed to comply with obligations under this Proclamation;

c) the licensed person has breached a condition of the license;

d) the licensed person has made a false or misleading statement to the Authority;

e) for a licensed manufacturer, the factory, or plant or equipment, specified in the license is no longer adequate to manufacture or secure excisable goods.

2/ Where a license is suspended under Sub-Article (1) of this Article, the Authority shall serve the licensed person with written notice of the suspension.

3/ The suspension of a license shall take effect from the date of service of the notice under Sub-Article (2) of this Article.

4/ A person served with a notice of suspension under Sub-Article (2) may, by notice in writing and within 14 days of service of the notice, or within such further time as the Authority may allow, appeal against the suspension to the tax complaint review department of the Authority.

www.chilot.me

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) መሠረት ፈቃድ የተሰጠው ሰው ዕግዱን በመቃወም የይግባኝ ማመልከቻ ያቀረበ እንደሆነ፣ የታክሱ ባለሥልጣን የይግባኝ ማመልከቻው በደረሰው በ፲፬ ቀናት ውስጥ:-

ሀ) የይግባኙን አቤቱታ በመቀበል የፈቃዱን ዕገዳ ሊያነሳ፤

ለ) ፈቃዱ የታገደበት ሰው ዕግዱ እንዲነሳለት ለማድረግ ለዕግዱ ምክንያት የሆኑ ጉድለቶችን በማሟላት ረገድ በማስታወቂያው በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ሊያከናውናቸው የሚገባ ተግባራትን የሚገልጽ ማስታወቂያ እንዲደርሰው በማድረግ፣ በማስታወቂያው በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ተግባራቱን ካከናወነ ዕግዱን የማንሳት፤

ሐ) ይግባኙን ውድቅ ማድረግና በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፩ መሰረት ፈቃዱን መሰረዝ ይችላል፡፡"

፮/ የታክሱ ባለሥልጣን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፭) በተመለከተው ጊዜ ውስጥ በንዑስ አንቀጹ የተመለከቱትን እርምጃዎች ካልወሰደ የፈቃዱ ዕገዳ እንደተነሳ ይቆጠራል፡፡

**፳፩. ፈቃድን ስለመሠረዝ**

፩/ የታክሱ ባለሥልጣን በሚከተሉት ሁኔታዎች በጽሁፍ ማስታወቂያ በመስጠት ፈቃዱን ሊሠርዝ ይችላል:-

ሀ) የታክስ ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፱ (፪) (ሀ) መሠረት ማስታወቂያ የደረሰው ከሆነ፤

ለ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳(፬) በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ፈቃድ የተሰጠው ሰው የፈቃዱን ዕገዳ በመቃወም ይግባኝ ያላቀረበ ከሆነ፤

ሐ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳ (፭) (ለ) በተሰጠው ማስታወቂያ ወይም በታክሱ ባለሥልጣን በተሰጠ ተጨማሪ ጊዜ ውስጥ ፈቃድ የተሰጠው ሰው በማስታወቂያው የተመለከተውን ሳያሟላ የቀረ እንደሆነ፤

መ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳ (፭) (ሐ) በተደነገገው መሠረት ፈቃዱ በመታገዱ ምክንያት የቀረበውን ይግባኝ የታክስ ባለሥልጣኑ ውድቅ ያደረገው ከሆነ፡፡

፪/ የፈቃድ መሠረዝ ተፈፃሚ የሚሆነው ፈቃዱ መሠረዙን በሚገልጸው ማስታወቂያ ከተመለከተው ቀን ጀምሮ ነው፡፡

5/ Where a licensed person lodges a notice of appeal in accordance with Sub-Article (4) of this Article, the Authority shall, within 14 days after receipt of the notice, either:

a) accept the appeal and revoke the suspension of the license;

b) provide the licensed person with written notice of the action required to be taken before the date specified in the notice to remedy the deficiencies that led to the suspension of the license and revoke the suspension if the action is taken within the specified time; or

c) reject the appeal and cancel the license in accordance with Article 21 of this proclamation.

6/ If the Authority fails to take action under Sub-Article (5) of this Article within the time specified in that Sub-Article, the suspension shall stand revoked.

**21. Cancellation of License**

1/ The Authority shall, by notice in writing, cancel the license of a person when:

a) the Authority has received notification under Article 19 (2) (a);

b) the person fails to appeal the suspension of the license within the time specified in Article 20 (4);

c) the person fails to comply with a notice served on the person under Article 20 (5) (b) within the time specified in the notice or within such further time as the Authority may allow;

d) the Authority rejects an appeal against the suspension of a license under Article 20 (5) (c).

2/ The cancellation of a license takes effect from the date specified in the notice of cancellation.

www.chilot.me

፫/ ፈቃድ ለተሰጠው ሰው የተሰጠው ፈቃድ መሠረዝ የኤክሳይዝ ታክስ መክፈልን እና የኤክሳይዝ ታክስ ማስታወቂያ ማቅረብን ጨምሮ ፈቃዱ ፀንቶ በነበረበት ጊዜ ባከናወነው ወይም ባላከናወነው ማናቸውም ተግባር ምክንያት በዚህ አዋጅ ወይም በታክስ አስተዳደር አዋጅ መሠረት የሚኖርበትን ተጠያቂነት አያስቀርም፡፡

## ፳፪.የፈቃድ መታገድ ወይም መሠረዝ የሚኖረው ውጤት

፩/ የተፈቀደለት አምራች የተሰጠው ፈቃድ የታገደ ወይም የተሠረዘ እንደሆነ፣

ሀ) አምራቹ:-

(፩) የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸውን ዕቃዎች የማምረቱን ተግባር ወዲያውኑ ማቆም፣

(፪) የኤክሳይዝ ታክስ በተጣለባቸው በእጁ በሚገኙ እቃዎች ላይ ያልተከፈለውን የኤክሳይዝ ታክስ ወዲያውኑ መክፈል፣

(፫) ከታክሱ ባለሥልጣን በሚሰጠው መመሪያ መሠረት በአምራቹ ፋብሪካ ውስጥ የሚገኙ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ማስወገድ፣

አለበት፡፡

ለ) የታክሱ ባለሥልጣን:-

(፩) የተፈቀደለት አምራች በፋብሪካው ውስጥ የሚገኙ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች በታክሱ ባለሥልጣን ወደፀደቀ ቦታ እንዲያዘዋውር የማዘዝ፣ እና

(፪) በዚህ አዋጅ የተደነገጉ ግዴታዎች መፈፀማቸውን ለማረጋገጥ እና የመንግሥትን ገቢ ለመሰብሰብ አስፈላጊ እስከሆነ ድረስ የታክሱ ባለሥልጣን በታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀጽ ፵፩ መሠረት የአምራቹን ፋብሪካ እና በፋብሪካው ውስጥ የሚገኙ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች መያዝ፣ ይችላል፡፡

፪/ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን አገልግሎቶች ለማቅረብ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ፈቃዱ የታገደ ወይም የተሠረዘ እንደሆነ ባለፈቃዱ:-

ሀ) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበትን አገልግሎት ማቅረቡን ማቆም፤ እና

ለ) የኤክሳይዝ ታክስ በሚከፈልባቸው አገልግሎቶች ላይ ያልተከፈለውን ታክስ መክፈል፣

3/ Any obligation or liability of a licensed person under this Proclamation or the Tax Administration Proclamation in respect of anything done or omitted to be done by the person while licensed, including the obligation to pay excise tax or to file excise tax returns, shall not be affected by cancellation of the person's license.

## 22. Consequences of Suspension or Cancellation of License

1/ If the license of a licensed manufacturer is suspended or cancelled:

a) the manufacturer shall:

(1) immediately cease to manufacture excisable goods;

(2) immediately pay all excise tax on excisable goods on hand in respect of which tax is still unpaid;

(3) dispose of excisable goods and materials in the manufacturer's factory in accordance with the direction of the Authority;

b) the Authority may:

(1) require the licensed manufacturer to remove excisable goods in the manufacturer's factory to another place approved by the Authority; and

(2) take control of the manufacturer's factory and seize any excisable goods at the factory as may be necessary in accordance with Article 41 of the Tax Administration Proclamation for the protection of revenue and ensure compliance with this Proclamation.

2/ If the license of a person licensed to supply excisable services is suspended or cancelled, the person shall:

a) cease to supply the excisable services; and

b) pay excise tax on excisable services supplied in respect of which tax is still unpaid.

www.chilot.me

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተፈፃሚ ከሚሆንባቸው ውጭ ያለ አስመጪ ፈቃዱ የታገደ ወይም የተሰረዘ እንደሆነ ፈቃድ የተሰጠበትን የሥራ እንቅስቃሴ ወዲያውኑ ማቆም አለበት፡፡

፬/ የታክስ ባለሥልጣኑ በፈቃዱ መታገድ ወይም መሠረዝ ምክንያት ያወጣውን ወጪ እንዲተካ ፈቃድ ለተሰጠው ሰው የጽሁፍ ማስታወቂያ ሊሰጠው ይችላል፡፡ የዚህ ዓይነቱ ወጪ ለታክስ አስተዳደር አዋጅ አፈጻጸም እንደታክስ ይቆጠራል፡፡

**፳፫. ፈቃድ ከመታገዱ ወይም ከመሠረዙ በፊት የታክስ ባለሥልጣኑ ሊሰጥ ስለሚገባው ማስጠንቀቂያ**

፩/ የታክስ ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ መሠረት የተሰጠውን ፈቃድ ለማገድ ወይም ለመሠረዝ ያቀደ እንደሆነ፣ ባለፈቃዱ ሊወሰድ የታቀደውን እርምጃ እንዲያውቀው ከ፳፩ ቀናት በፊት የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ መስጠት አለበት፡፡ ይህም ማስጠንቀቂያ እርምጃው እንዲወሰድ መንስኤ የሆኑትን ሁኔታዎች እና ፈቃድ የተሰጠው ሰው ማስተካከያ ሊያደርግባቸው የሚገባ ጉዳዮችን ጭምር የሚገልጽ መሆን አለበት፡፡

፪/ ፈቃድ የተሰጠው ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ማስጠንቀቂያው በደረሰው በ፳፩ ቀናት ውስጥ በታክሱ ባለሥልጣን የተጠየቁ የማስተካከያ እርምጃዎችን መውሰድ አለበት፡፡

፫/ የታክስ ባለሥልጣኑ ፈቃድ የተሰጠው ሰው የወሰዳቸውን የማስተካከያ እርምጃዎች የሚመለከት ሪፖርት በደረሰው በ፲፬ ቀናት ውስጥ የተወሰዱት እርምጃዎች በቂ መሆናቸውን ወይም በማስጠንቀቂያው የተገለፁ እርምጃዎች የሚወሰዱ መሆኑን ለመግለጽ ይችላል፡፡

፬/ በማስጠንቀቂያው የተገለፁ እርምጃዎች የሚወሰዱ መሆኑን እንዲያውቀው የተደረገ ፈቃድ የተሰጠው ሰው በታክስ ባለሥልጣኑ ውሳኔ ቅር የተሰኘ እንደሆነ፣ ውሳኔው ከተገለፀለት ቀን ጀምሮ በ፲ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለታክስ ባለሥልጣኑ የአቤቱታ አጣሪ የሥራ ክፍል ሊያቀርብ ይችላል፡፡

፭/ የአቤቱታ አጣሪ የሥራ ክፍል አቤቱታው በደረሰው በ፲ ቀናት ውስጥ በቀረበው ቅሬታ ላይ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡

3/ If the license of an importer, other than a person to whom Sub-Article (2) of this Article applies, is suspended or cancelled, the person shall immediately cease to undertake the activity for which the license is issued.

4/ The Authority may, by notice in writing, require a licensed person to pay such costs as may be incurred by the Authority as a result of the suspension or cancellation of the person's license as specified in the notice and the costs shall be treated as tax for the purposes of the Tax Administration Proclamation.

**23. Authority to Notify Licensee Prior to Suspension, Revocation or Cancellation of a License**

1/ Where the Authority seeks to suspend, revoke or cancel a license under this Proclamation, it shall give 21 days' notice to the licensee prior to taking the intended action, giving the grounds upon which such intended action shall be taken, and requiring the licensee to remedy any circumstances which may require to be remedied.

2/ The licensee shall, within 21 days of receipt of the notice, take actions as required by the Authority.

3/ The Authority shall, within 14 days, acknowledge in writing the actions taken by the licensee or proceed to confirm the effect of the intended notified action.

4/ A Licensed Person who receives notification of confirmation of the intended action is dissatisfied with the decision of the Authority may file a notice of objection with the tax compliant Review Department of the Authority within 10 days from receipt of such decision.

5/ The Review Department shall make a decision on the notice of objection within 10 days from receipt of such notice.

www.chilot.me

፮/ ፈቃድ የተሰጠው ሰው በአቤቱታ አጣሪ የሥራ ክፍል በተሰጠው ውሣኔ ቅር የተሰኘ እንደሆነ ውሣኔው በተገለፀለት በ፲፬ ቀናት ውስጥ ለግብር ይግባኝ ኮሚሽን ይግባኝ ሊያቀርብ የሚችል ሲሆን፣ የይግባኙ ማመልከቻ በ፯ ቀናት ውስጥ ለታክሱ ባለሥልጣን እንዲደርስ ማድረግ አለበት፡፡

**፳፬. ስለይግባኝ**

፩/ የግብር ይግባኝ ኮሚሽን በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፫ (፮) መሠረት የቀረበለትን ይግባኝ በታክስ አስተዳደር አዋጅ በተደነገገው ጊዜ ውስጥ መርምሮ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡

፪/ በግብር ይግባኝ ኮሚሽን የተሰጠው ውሳኔ የሕግ ስህተት አለበት ብሎ የሚያምን ፈቃድ የተሰጠው ሰው ወይም የታክስ ባለሥልጣን ውሳኔው በተሰጠ በ፴ ቀናት ውስጥ ይግባኙን ለፌደራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት ሊያቀርብ ይችላል፡፡

## ምዕራፍ አራት
## የኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር

**፳፭. የኤክሳይዝ ታክስ በሚከፈልባቸው ዕቃዎች ላይ የሚደረግ ቁጥጥር**

፩/ ፈቃድ በተሰጠው አምራች ፋብሪካ ውስጥ የሚገኙ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች በታክስ ባለሥልጣኑ የኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር (ከዚህ በኋላ "የኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር" በሚል የሚጠራ) ይደረግባቸዋል፡፡

፪/ በዚህ አዋጅ መሠረት የኤክሳይዝ ታክስ በሚከፈልባቸው ዕቃዎች ላይ የኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር የሚደረገው ከሚከተሉት በቀደመው ጊዜ ይሆናል:-

ሀ) ፈቃድ በተሰጠው አምራች ፋብሪካ ውስጥ የሚገኙ ዕቃዎች በኢትዮጵያ ውስጥ ጥቅም ላይ እንዲውሉ ከፋብሪካው እስከሚወጡ፤

ለ) ዕቃዎቹ ከኢትዮጵያ ውጭ እስከሚላኩ፤ ወይም

ሐ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) ወይም በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፰ (፩) (ሸ) መሠረት ዕቃዎቹ ከአገልግሎት ውጭ እስከሚደረጉ ወይም እስከሚወገዱ ድረስ፡፡

፫/ ዕቃዎች በኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር ስር እስካሉ ድረስ:-

6/ A Licensed Person dissatisfied with the decision of the Review Department may file a notice of appeal with the Tax Appeal Commission with 14 days after being served with a notice of decision and shall serve the Authority with the appeal application within 7 days of filing.

**24. Appeal**

1/ The Tax Appeal Commission shall hear and determine the appeal made in accordance with Article 23 (6) of this Proclamation within the time prescribed by the Tax Administration Proclamation.

2/ Any party aggrieved by the decision of the Tax Appeal Commission may appeal to the Federal High Court on question of law within 30 days from the date of the decision.

## CHAPTER FOUR
## EXCISE TAX CONTROL

**25. Excisable Goods under Excise Control**

1/ Excisable goods stored in the factory of a licensed manufacturer shall be subject to the control of the Authority (herein after referred to as "excise control").

2/ Excisable goods shall be subject to excise control until the earlier of:

a) the removal of the goods from the factory of a licensed manufacturer for consumption in Ethiopia;

b) until the goods are export from Ethiopia; or

c) the destruction or disposal of goods in accordance with Sub-Article (4) of this Article or Article 8 (1) (h) of this Proclamation.

3/ When goods are subject to excise control:

www.chilot.me

ሀ) በታክስ ባለሥልጣኑ ሥልጣን የተሰጠው የባለሥልጣኑ ሠራተኛ በማናቸውም ጊዜ ዕቃዎቹን መመርመር ይችላል፡፡

ለ) በዚህ አዋጅ መሠረት በታክሱ ባለሥልጣን ከተፈቀደለት ሰው በስተቀር ማናቸውም ሰው ዕቃዎቹን ከፋብሪካ ማውጣት ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ ዕቃዎቹን የሚመለከት ማናቸውንም ተግባር መፈፀም አይችልም፡፡

a) an officer authorized by the Authority may, at any time, examine the goods.

b) no person shall, except with authority of the Authority granted in accordance with this Proclamation, remove the goods from a factory or otherwise interfere in any way with the goods.

፬/ ዕቃዎች በኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር ስር ባሉበት ጊዜ የታክሱ ባለሥልጣን የዕቃው ባለቤት ዕቃዎቹን ለታክሱ ባለሥልጣን እንዲያስረክብ ሊጠይቅ ይችላል፡፡ የታክሱ ባለሥልጣን ዕቃዎቹን ከተረከበ በኋላ ዕቃዎቹ በታክሱ ባለሥልጣን በሚሰጥ መመሪያ መሠረት በባለቤቱ ወጪ ሊሸጡ ወይም ከአገልግሎት ውጭ እንዲሆኑ ሊደረግ ወይም ሊወገዱ ይችላል፡፡

4/ When goods are subject to excise control, the Authority may permit the owner of those goods to abandon them to the Authority, and on such abandonment the goods may, at the expense of the owner thereof, be destroyed or otherwise disposed of as the Authority may direct.

## ፳፮. <u>በኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር ሥር ያሉ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች በሚመለከት ፈቃድ የተሰጠው አምራች ግዴታዎች</u>

## 26. **<u>Obligations of Licensed Manufacturer in Relation to Excisable Goods under Excise Control</u>**

፩/ የኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር የሚደረግባቸው የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች በተገቢው የሂሳብ አያያዝ የተመዘገቡ መሆኑን ለማረጋገጥ፣ የተፈቀደለት አምራች፡-

ሀ) የታክሱ ባለሥልጣን በፋብሪካው ውስጥ የሚገኙ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ወይም ጥሬ ዕቃዎችን ለመመዝገብ፣ ክብደታቸውን ለመለካት፣ ለመቆጣጠር፣ ለመቁጠር እንዲችል ወይም እንደአስፈላጊነቱ ሌሎች ተመሳሳይ የቁጥጥር ሥራዎችን እንዲያከናውን በፋብሪካው ውስጥ የመለኪያ ወይም የመቁጠሪያ መሣሪያዎች እንዲኖሩ እና በሚገባ እንዲጠበቁ የማድረግ፤

ለ) በፋብሪካው ውስጥ የሚገኙ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች የተሟላ ቁጥጥር ለማድረግ በሚያስችል መንገድ የማስቀመጥ፤

ሐ) በፀደቀው ቅጽ መሠረት የጥሬ ዕቃዎችን ምዝገባ ማካሄድ፣ በተለይም በማምረት ሂደት ጥቅም ላይ እንዲውሉ ፋብሪካው የተረከባቸውን ጥሬ ዕቃዎች እና ግብአቶች በእነዚህ ቅፆች ላይ መመዝገብ እና በየወሩ መጨረሻ የምዝገባውን ሚዛን ትክክለኛነት የማረጋገጥ፤

1/ For the purposes of ensuring proper accounting of excisable goods under excise control, a licensed manufacturer shall:

a) keep and maintain at the factory, metering and measuring devices, and such other equipment as may be necessary in order to enable the Authority to take an account of, or check by weight, gauge or measure, all excisable goods or materials in the factory;

b) store excisable goods in the factory in such manner as to facilitate the taking of a full account of the goods;

c) keep a materials account in the approved form and enter therein the particulars of all raw materials and intermediate goods received at the factory for use in manufacturing, and balance the account at the end of each month;

www.chilot.me

መ) በፀደቀው ቅጽ መሠረት የመጨረሻ ምርቶችን ምዝገባ ማከናወን፣ እና በዚሁ ቅጽ ላይ በፋብሪካው የተመረተ፣ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች እና ከፋብሪካው የወጡ ዕቃዎችን መመዝገብ እና በየወሩ መጨረሻ የምዝገባውን ሚዛን ትክክለኛነት የማረጋገጥ፤

ሠ) የኤክሳይዝ ታክስ በሚከፈልባቸው በፋብሪካው ውስጥ ጥቅም ላይ በዋሉ ዕቃዎች ላይ የኤክሳይዝ ታክስ የተከፈለ መሆኑን የማረጋገጥ፤

ረ) ሚኒስትሩ በሚያወጣው መመሪያ እንዲሟሉ የሚጠየቁ ሁኔታዎችን የማሟላት፤

ግዴታ አለበት፡፡

፪/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) (ሀ) አፈፃፀም የታክሱ ባለሥልጣን በሚያወጣው መመሪያ ተፈላጊ የሆኑ የመለኪያ ወይም የመቆጣሪያ እንዲሁም ሌሎች አስፈላጊ መሣሪያዎችን ተፈላጊ ባህሪያት ሊወስን ይችላል፡፡

፫/ የታክሱ ባለሥልጣን፦

ሀ) ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው በማናቸውም ጊዜ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ናሙና ከአምራቹ በነፃ የመውሰድ መብት ያለው ሲሆን፣ እነዚህ ናሙናዎች የታክስ ባለሥልጣኑ በሚሰጠው ውሳኔ መሠረት ሊወገዱ ወይም ለአምራቹ ሊመለሱ ይችላሉ፡፡

ለ) በጽሁፍ በሚወስነው አኳኋን የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ባለቤት የኤክሳይዝ ታክሱን ሳይከፍል ለገበያ በማይውል መጠን ከፋብሪካው ናሙናዎችን እንዲወስድ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

**፳፯. <u>ከአልኮል ማጣሪያ ፋብሪካ ውጭ የአልኮል ማጣሪያ መሣሪያን መያዝ ወይም መጠቀም የተከለከለ ስለመሆኑ</u>**

፩/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ፈቃድ ከተሰጠው የአልኮል ማጣሪያ ፋብሪካ ውጭ ማናቸውም ሰው የአልኮል ማጣሪያ መሣሪያን መያዝ ወይም መጠቀም አይችልም፡፡

d) keep a finished goods account in the approved form and enter therein particulars of all excisable goods manufactured therein and delivered therefrom and shall balance the account at the end of each month;

e) ensure that excise tax is paid on any excisable goods consumed at the factory; and

f) comply with such other requirements as may be specified in the directive issued by the Minister.

2/ For the purpose of Sub-Article (1)(a) of this Article, the Authority shall, by a directive, specify the requirements of a measuring or metering device and such other equipment as may be required.

3/ The Authority:

a) may, at any time, take samples of excisable goods free of charge for such purposes of the Proclamation as the Authority may deem necessary, and any such samples shall be disposed of or returned to the Manufacturer as the Authority may direct; or

b) may, subject to such written conditions as the Authority may impose, permit the owner of excisable goods to take samples which are of no commercial value without payment of the excise tax thereon.

**27. <u>Keeping or Use of Still otherwise than by Distiller or Rectifier Prohibited</u>**

1/ without prejudice to the provision of Sub-Article (2) of this Article, no person other than a licensed distiller or rectifier shall keep or use a still.

www.chilot.me

፪/ የታክሱ ባለሥልጣን የሚጥላቸው አስገዳጅ ሁኔታዎች እንደተጠበቁ ሆነው በሚከተሉት ምክንያቶች ባለሥልጣኑ ከተፈቀደለት የአልኮል ማጣሪያ ፋብሪካ ውጭ ሌላ ሰው የአልኮል ማጣሪያ መሣሪያ እንዲይዝ ወይም እንዲጠቀምበት ባለሥልጣኑ ሊፈቅድ ይችላል:-

ሀ) የአልኮል ማጣሪያ መሣሪያን ለሽያጭ የሚያመርት ወይም የሚይዝ ሲሆን፤

ለ) መሣሪያው የተያዘው ወይም ጥቅም ላይ የሚውለው ለሙከራ፣ ለጥናት፣ ወይም ለሳይንሳዊ ምርምር ዓላማ ሲሆን፤

ሐ) የአልኮል ማጣሪያ መሣሪያው የተያዘው ወይም ጥቅም ላይ የሚውለው ከአልኮል መጠጦች ውጭ የሆነ ሌላ ምርት ለማምረት ሲሆን፡፡

2/ The Authority may permit, without prejudice to such conditions as the Authority may impose, the keeping or use of a still by a person other than a licensed distiller or rectifier when the still is:

a) kept by a person who makes or keeps stills solely for the purpose of sale;

b) kept or used for experimental, analytical, or scientific purposes;

c) kept or used for the manufacture of an article other than spirits.

## ፳፰. ከፋብሪካ ወጪ እንደተደረጉ የሚቆጠሩ ዕቃዎች

፩/ የተፈቀደለት አምራች የታክሱን ባለሥልጣን በሚያረካ አኳኋን በፋብሪካው የተመረተውን የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበት ዕቃ ብዛት በማስረጃ ማረጋገጥ ያልቻለ እንደሆነ፣ በአንድ ወር ውስጥ ተመርቷል በተባለው እና ሊመረት ይችላል ተብሎ በሚታመነው መካከል ያለውን ዕቃ ከኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር ውጭ ከፋብሪካው ወጪ እንዳደረገ ይቆጠራል፡፡

፪/ የተፈቀደለት አምራች በትክክል ባመረተው እና የተመረተ ዕቃ በሚመዘገብበት ሰነድ ላይ በተመዘገበው መካከል ልዩነት መኖሩን ያወቀ እንደሆነ፣ ይህንኑ ወዲያውኑ ለታክሱ ባለሥልጣን ማስታወቅ አለበት፡፡

## 28. Deemed Removal of Excisable Goods

1/ A licensed manufacturer who cannot account, to the satisfaction of the Authority, for any quantity of excisable goods manufactured shall be deemed to have removed those goods from excise control in the month in which the discrepancy arose.

2/ A licensed manufacturer shall notify the Authority of any discrepancies between the manufacturer's actual and recorded inventory as soon as the manufacturer becomes aware of the discrepancy.

# ምዕራፍ አምስት
# የኤክሳይዝ ቴምብር

## ፳፱. የኤክሳይዝ ቴምብር እና ሌሎች ምልክቶች

፩/ ሚኒስትሩ በሚያወጣው መመሪያ የሚከተሉትን ሊወስን ይችላል:-

ሀ) የኤክሳይዝ ቴምብር ሊለጠፍባቸው የሚገባ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች፤

ለ) ከኤክሳይዝ ታክስ ነፃ በሆኑ የአልኮል ምርቶች ላይ ሊደረግ የሚገባውን ምልክት፤

ሐ) የኤክሳይዝ ቴምብር እና ሌሎች ምልክቶች የሚለጠፉባቸውን የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች የአስተዳደር ሥርዓት፤

# CHAPTER FIVE
# EXCISE STAMPS

## 29. Excise Stamps and other Markings

1/ The Minister may by directive specify:

a) the excisable goods to which excise stamps shall be affixed;

b) the markings that shall be affixed on spirits that are exempt from Excise Tax;

c) the systems for management of excise stamps and excisable goods;

www.chilot.me

መ) የኤክሳይዝ ቴምብር ወይም ሌሎች ምልክቶች የሚለጠፉበትን ቦታ እና ጊዜ፡፡

፪/ የታክሱ ባለሥልጣን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የኤክሳይዝ ቴምብር እና ሌሎች ምልክቶች እንዲለጠፍባቸው በታዘዙ ዕቃዎች ላይ የሚለጠፈውን የኤክሳይዝ ቴምብር እና ሌሎች ምልክቶች ዓይነት እና ይዘት በሚመለከት አገራዊ ተነባቢነት ባላቸው ሁለት ጋዜጣዎች ቢያንስ ለሁለት ጊዜ ያህል ማስታወቂያ ያወጣል፡፡

፫/ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች የተመረቱት ለውጭ ገበያ እንዲላኩ ወይም ከዚህ አዋጅ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ፪ በተራ ቁጥር ፪ እና ፫ ለተዘረዘሩ ሰዎች የሆነ እንደሆነ፣ በእነዚህ ዕቃዎች ላይ ለሚደረገው ክትትልና ቁጥጥር እንዲያመች ሚኒስትሩ በሚወስነው አኳኋን በዕቃዎቹ ላይ ልዩ ምልክት ሊደረግ ይገባል፡፡

፬/ ሚኒስትሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የኤክሳይዝ ቴምብር ከመለጠፉ በፊት ማናቸውም ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተዘረዘሩትን የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች የኤክሳይዝ ቴምብር እንዲለጠፍባቸው ከተቀመጡበት ቦታ ማንቀሳቀስ አይችልም፡፡

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) የተመለከተው ቢኖርም የታክሱ ባለሥልጣን በተለዩ ሁኔታዎችና ከሚኒስትሩ አስቀድሞ ፈቃድ የተገኘ ሲሆን የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች የኤክሳይዝ ቴምብር ሳይለጠፍባቸው ከኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር ውጭ እንዲሆኑ ሊያደርግ ይችላል፡፡

## ምዕራፍ ስድስት

## ስለተመላሽ

**፴. ተመላሽ**

፩/ በአገር ውስጥ የተመረቱ ወይም ከውጭ አገር የመጡ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች የኤክሳይዝ ታክስ ከተከፈለባቸው በኋላ ከሚከተሉት ሁኔታዎች አንዱ ያጋጠመ መሆኑን የታክሱ ባለሥልጣን ያረጋገጠ እንደሆነ፣ በአምራቹ ወይም በአስመጪው በሚቀርብ የፅሑፍ ማመልከቻ መሠረት የተከፈለው የኤክሳይዝ ታክስ ተመላሽ ሊደረግ ይችላል:-

d) the place and time of affixing excise stamps.

2/ The Authority shall, by notices to be issued two times in at least two newspapers of national circulation, specify the types and descriptions of excise stamps to be affixed on goods specified under Sub-Article (1) of this Article.

3/ If excisable goods are manufactured for export, or for delivery to persons listed in No. (2) and (3) of the Second Schedule, the goods shall be marked with such inscriptions as the Minister may specify to facilitate the tracking and tracing of the goods.

4/ A person shall not remove excisable goods specified in Sub-Article (1) from the place designated for affixing stamps unless the goods have been affixed with stamps in accordance with the directive.

5/ Notwithstanding Sub-Article (4) the Authority may in exceptional circumstances, and with prior approval of the Minister, allow removal of excisable goods from excise control without affixing excise stamps on the goods.

## CHAPTER SIX

## REFUNDS

**30. Refunds**

1/ If excise tax has been paid by a person on excisable goods manufactured in, or imported into Ethiopia, the Authority shall, on written application by the person, refund the excise tax paid if satisfied that:

www.chilot.me

ሀ) በኢትዮጵያ ውስጥ ጥቅም ላይ ከመዋላቸው በፊት:-

(፩) ወደኢትዮጵያ በመጓጓዝ ላይ እያሉ ዕቃዎቹ ከጥቅም ውጭ የሆኑ ወይም የተሠረቁ እንደሆነ፣

(፪) በኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር ስር ያሉ ዕቃዎች ከጥቅም ውጭ የሆኑ ወይም የተሠረቁ እንደሆነ፣

(፫) በሽያጭ ውሉ መሠረት ገዢው ዕቃውን ለሻጩ የመለሰ እንደሆነ፡፡

ለ) የኤክሳይዝ ታክስ ከተከፈለ በኋላ ፈቃድ በተሰጠው ወይም በተመዘገበ አምራች ከኤክሳይዝ ታክስ ነፃ የሆኑ ዕቃዎችን ለማምረት የዋሉ እንደሆነ፡፡

፪/ የተፈቀደለት ሰው የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተዘረዘሩትን ሁኔታዎች የሚያሟሉ እንዲሁም የኤክሳይዝ ታክሱን የከፈለ እና ለእነዚህ ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ከገዢው ምንም ዓይነት ክፍያ ያልተቀበለ መሆኑን በማስረጃ ማረጋገጥ የቻለ እንደሆነ፣ የኤክሳይዝ ታክሱ ተመላሽ እንዲደረግለት ለባለሥልጣኑ በጽሑፍ ማመልከቻ ሊያቀርብ ይችላል፡፡ የታክሱ ባለሥልጣንም የተፈቀደለት ሰው በእነዚህ ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ላይ ምንም ዓይነት የኤክሳይዝ ታክስ ያልተቀበለ መሆኑን ሲያረጋግጥ የተከፈለው የኤክሳይዝ ታክስ ተመላሽ እንዲሆን ሊያደርግ ይችላል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የሚቀርበው የተመላሽ ጥያቄ ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት በቀደመው ጊዜ ውስጥ መቅረብ አለበት:-

ሀ) ዕቃዎቹ ወይም አገልግሎቶቹ ከተሸጡበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር የአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ፣ ወይም

ለ) ገዢው በሕግ የከሠረ መሆኑ በተረጋገጠበት ጊዜ፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ መሠረት የኤክሳይዝ ታክስ ተመላሽ እንዲሆን የሚቀርበው ማመልከቻ:-

ሀ) በፀደቀው ቅጽ መሠረት፣ እና

a) before being consumed or used in Ethiopia:

(1) the goods have been damaged or stolen during the voyage or transportation to Ethiopia;

(2) the goods have been damaged or stolen while subject to excise control;

(3) the buyer has returned the goods to the seller in accordance with the contract of sale.

b) excisable goods that have subsequently been used by a licensed or registered manufacturer to manufacture unexcitable goods after excise tax has been paid;

2/ A licensee may apply to the Authority for a refund of excise tax if the excisable goods or excisable services satisfy the conditions stated in Sub-Article (1) of this Article and he has paid and accounted for excise tax on such goods or services but has not received any payment from the purchaser for the goods or services, and the Authority may refund the excise tax if satisfied that payment for the goods or services has not been received.

3/ An application for a refund under Sub-Article (2) of this Article may be made on the earlier of:

a) one year from the date of the sale of the goods or services; or

b) the purchaser becoming legally insolvent.

4/ An application for a refund under this Article shall be:

a) in the prescribed form; and

www.chilot.me

ለ) በታክሱ ባለሥልጣን በሚወሰነው አኳኋን ሆኖ፣ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚቀርብ የተመላሽ ጥያቄን በሚመለከት የኤክሳይዝ ታክሱ በተከፈለ በ፲፪ ወራት ውስጥ መቅረብ አለበት፡፡

፭/ በዚህ አንቀጽ መሠረት ተመላሽ የሚደረገው የኤክሳይዝ ታክስ መጠን የሚወሰነው በታክስ አስተዳደር አዋጅ በተደነገገው መሠረት ይሆናል፡፡

፮/ ወደአገር ውስጥ ከገቡ በኋላ ተመልሰው ወደውጭ አገር በተላኩ ዕቃዎች ላይ የኤክሳይዝ ታክስ የተከፈለ ከሆነ ወደውጭ አገር በተላኩት ዕቃዎች ላይ የተከፈለው ታክስ በጉምሩክ አዋጅ በተደነገገው መሠረት ተመላሽ ይደረጋል፡፡

፯/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፭ መሠረት የኤክሳይዝ ታክስ ተመላሽ ከተደረገ በኋላ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ከገዢው ላይ የኤክሳይዝ ታክሱን በሙሉ ወይም በከፊል የተቀበለ ከሆነ፣ የኤክሳይዝ ታክሱን በተቀበለ በ፴ ቀናት ውስጥ በተቀበለው መጠን ተመላሽ የተደረገለትን የኤክሳይዝ ታክስ ለታክሱ ባለሥልጣን መመለስ አለበት፡፡

**፴፩. <u>ተመላሽ የተከፈለባቸው የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች የተሸጡ ወይም ከተፈቀደበት ዓላማ ውጭ ጥቅም ላይ የዋሉ እንደሆነ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ስለመሆኑ</u>**

፩/ በዚህ አዋጅ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የተመላሽ ክፍያ የተፈፀመባቸው ኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ተመላሹ ከተከፈለ በኋላ የተሸጡ ወይም ተመላሹ ከተፈቀደበት ዓላማ ውጭ ጥቅም ላይ የዋሉ እንደሆነ፣ ተመላሹ ባይፈቀድ ኖሮ ዕቃዎቹ ላይ ሊከፈል ይገባ በነበረው ልክ የኤክሳይዝ ታክስ ይከፈልባቸዋል፡፡

፪/ ለማናቸውም ዓላማ የኤክሳይዝ ታክስ ተመላሽ ክፍያ የተፈፀመበት ዕቃ በእጁ የገባ ሰው፣ ዕቃውን ተመላሹ ከተፈቀደበት ዓላማ ውጭ ለመጠቀም ወይም ለመሸጥ፣ የፈለገ እንደሆነ፣ ዕቃው የሚሸጥበትን ወይም ጥቅም ላይ የሚውልበትን ዝርዝር ሁኔታ በሚመለከት ለታክሱ ባለሥልጣን ሪፖርት ማቅረብ እና በዕቃው ላይ ሊከፈል የሚገባውን የኤክሳይዝ ታክስ መክፈል አለበት፡፡

b) lodged with the Authority in the prescribed manner within 12 months from the date of payment of the excise tax, in the case of an application under Sub-Article (1) of this Article;

5/ The amount of a refund of excise tax payable under this Article shall be made in accordance with the Tax Administration Proclamation.

6/ If excise tax has been paid on the importation of excisable goods that have been subsequently exported the tax shall be refunded in accordance with the Customs Proclamation.

7/ If excise tax has been refunded under Sub-Article (5) of this Article and the licensed person has subsequently recovered the whole or part of the excise tax from the purchaser of the goods or services, the licensed person shall repay the refunded excise tax to the Authority to the extent that it has been recovered within 30 days of the recovery.

**31. <u>Excisable Goods Subject to a Refund Liable for Excise Tax on Disposal or Inconsistent Use</u>**

1/ without prejudice to the provision of this Proclamation, when excisable goods in respect of which a refund of excise Tax has been paid are subsequently disposed of, or used, in a manner inconsistent with the purpose for which the refund was granted, the goods shall be liable for the excise tax that would have been payable on the goods if the refund had not been granted.

2/ When a person who, being in possession of excisable goods in respect of which a refund of excise tax has been granted for any purpose, proposes to dispose of, or use, the goods for a purpose inconsistent with the purpose for which the refund was granted, the person shall furnish the Authority with the particulars of the proposed disposal or use, and shall pay the excise tax thereon.

www.chilot.me

**፴፪. ከኤክሳይዝ ታክስ ነፃ የተደረጉ ዕቃዎች ተመልሰው ወደ አገር ውስጥ የገቡ ወይም ለሽያጭ የዋሉ እንደሆነ ታክሱ የሚከፈል ስለመሆኑ**

፩/ በዚህ አዋጅ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ወደውጭ አገር ከተላኩ ወይም በዓለም አቀፍ ትራፊክ ለመንገደኞች አገልግሎት እንዲውሉ በአውሮፕላን ላይ ከተጫኑ በኋላ፣ ለአገር ውስጥ ፍጆታ እንዲውሉ በኢትዮጵያ ውስጥ ከጭነት የተራገፉ እንደሆነ፣ አስመጪው ዕቃዎቹ በተራገፉበት ጊዜ ፀንቶ ባለው የማስከፈያ መጣኔ መሠረት በእነዚህ ዕቃዎች ላይ የኤክሳይዝ ታክስ መክፈል አለበት፡፡

፪/ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ከታክሱ ነፃ ተደርገው ወደአገር ውስጥ ከገቡ ወይም ከተሸጡ በኋላ ተመልሰው ለሽያጭ ከዋሉ ወይም ከተፈቀደበት ዓላማ ውጭ ጥቅም ላይ የዋሉ እንደሆነ የኤክሳይዝ ታክስ ይከፈልባቸዋል፡፡

**፴፫. ከኤክሳይዝ ታክስ ነፃ የተደረጉ ዕቃዎች ተመልሰው የተሸጡ ወይም ከተፈቀደበት ዓላማ ውጭ የዋሉ እንደሆነ ታክሱ የሚከፈል ስለመሆኑ**

፩/ ማናቸውም ሰው ከዚህ አዋጅ ጋር በተያያዘው ሠንጠረዥ ፪ ከኤክሳይዝ ታክስ ነፃ የተደረጉ ዕቃዎችን ወደአገር ውስጥ ካስገባ ወይም ከገዛ በኋላ ዕቃዎቹን መልሶ የሸጠ ወይም ከተፈቀደበት ዓላማ ውጭ ጥቅም ላይ ያዋለ እንደሆነ ዕቃዎቹ በተሸጡበት ወይም ከተፈቀደበት ዓላማ ውጭ ጥቅም ላይ በዋሉበት ቀን ፀንቶ በሚሠራበት የማስከፈያ ልክ መሠረት የኤክሳይዝ ታክስ መክፈል አለበት፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም ከኤክሳይዝ ታክስ ነፃ ሆነው ወደአገር ውስጥ የገቡ ተሽከርካሪዎችን በሚመለከት ከታክስ ነፃ መብት የተሰጠው የተፈጥሮ ሰው የሞተ እና ተሽከርካሪው በውርስ ለወራሾች የተላለፈ ከሆነ የኤክሳይዝ ታክሱ አይከፈልም፡፡

## ምዕራፍ ሰባት
## የኤክሳይዝ ታክስ አስተዳደር

**፴፬. የታክስ አስተዳደር አዋጅ ተፈፃሚነት**

በዚህ አዋጅ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የታክስ አስተዳደር አዋጅ የኤክሳይዝ ታክስ አስተዳደርን በሚመለከት ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

**32. Exempt Excisable Goods Liable for Excise Tax on Re-importation or Purchase**

1/ without prejudice to the provision of this Proclamation when excisable goods that have been exported for use as stores on an aircraft operating in international traffic are subsequently unloaded in Ethiopia for home use, the importer shall be liable to pay excise tax on such goods at the rate in force at the time of unloading.

2/ Excisable goods imported or purchased free of excise tax shall be liable for excise tax on disposal or inconsistent use.

**33. Exempt Excisable Goods Liable for Excise Tax on Disposal or Inconsistent Use**

1/ When a person imports or purchases excisable goods which are exempt from excise tax under the Second Schedule and the person subsequently disposes of, or uses, the goods in a manner inconsistent with the exemption, the person shall be liable to pay excise tax on the goods at the rate applicable to goods of that class or description at the time of disposal or inconsistent use.

2/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (1) of this Article in the case of a motor vehicle, excise tax shall not be payable where in the case of a natural person, that person dies and the ownership of the motor vehicle is transferred by way of bequest to or inheritance by another person.

## CHAPTER SEVEN
## EXCISE TAX ADMINISTRATION

**34. Application of Tax Administration Proclamation**

The Tax Administration Proclamation shall subject this Proclamation apply for the purposes of the administration of this Proclamation.

www.chilot.me

**፴፭. <u>መዝገብ ስለመያዝ</u>**

በዚህ አዋጅ የኤክሳይዝ ታክስ የመክፈል ግዴታ የተጣለበት ማናቸውም ሰው በዚህ አዋጅ በተደነገገው እና ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የሂሳብ መዝገብ መያዝ ያለበት ሲሆን፣ የሚይዘውን የሂሳብ መዝገብ በታክስ አስተዳደር አዋጅ ለተመለከተው ጊዜ እና በተመለከተው አኳኋን ጠብቆ ማቆየት አለበት፡፡

**፴፮. <u>የኤክሳይዝ ታክስን ስለማስታወቅ</u>**

በማናቸውም አንድ ወር የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈል ቢሆንም ባይሆንም የተፈቀደለት አምራች የእያንዳንዱን ወር ሂሳብ የሚቀጥለው ወር ፴ኛው ቀን ከማለፉ በፊት በፀደቀው ቅጽ እና በታዘዘው አኳኋን ለታክሱ ባለሥልጣን ማስታወቅ አለበት፡፡

**፴፯.<u>የኤክሳይዝ ታክስን የመክፈል ግዴታን ስለመወጣት</u>**

፩/ የተፈቀደለት አምራች በአንድ ወር ውስጥ ከማምረቻው ፋብሪካ ወጪ ባደረጋቸው ዕቃዎች ላይ ሊከፍል የሚገባውን የኤክሳይዝ ታክስ የሚቀጥለው ወር ፴ኛው ቀን ከማለፉ በፊት ለታክሱ ባለሥልጣን ገቢ ማድረግ አለበት፡፡

፪/ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን አገልግሎቶች የሚያቀርብ ሰው በአንድ ወር ባቀረባቸው አገልግሎቶች ላይ ሊከፍል የሚገባውን ታክስ የሚቀጥለው ወር ፴ኛው ቀን ከማለፉ በፊት ለታክሱ ባለሥልጣን ገቢ ማድረግ አለበት፡፡

፫/ አስመጪው ወደአገር ውስጥ ባስገባቸው የኤክሳይዝ ታክስ በሚከፈልባቸው ዕቃዎች ላይ ሊከፍል የሚገባውን የኤክሳይዝ ታክስ ዕቃዎቹ ወደአገር ውስጥ በገቡበት ጊዜ ለታክሱ ባለሥልጣን መክፈል አለበት፡፡

፬/ ወደአገር ውስጥ በሚገቡ የኤክሳይዝ ታክስ በሚከፈልባቸው ዕቃዎች ላይ ታክሱ የሚሠላው፣ የሚከፈለው፣ ሂሳቡ የሚያዘው እና የታክሱ ዕዳ በአስገዳጅነት የሚሰበሰበው በጉምሩክ ሕግ መሠረት ይሆናል፡፡

**<u>ምዕራፍ ስምንት</u>**

**<u>የወንጀል ጥፋቶችና አስተዳደራዊ ቅጣቶች</u>**

**፴፰. <u>አስተዳደራዊ ቅጣት</u>**

፩/ ፈቃድ ሳይኖረው በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፭ (፩) (ሀ) እና (ለ) የተዘረዘሩትን ተግባራት የሚያከናውን ሰው የሚከተለውን አስተዳደራዊ ቅጣት ይቀጣል:-

**35. <u>Record keeping</u>**

A person liable to pay excise tax under this Proclamation shall keep such records as may be specified in this Proclamation or the directive to be issued by the Authority and shall retain the records for the time period and in the manner, specified in the Tax Administration Proclamation.

**36. <u>Excise Tax Returns</u>**

A licensed manufacturer or a supplier of excisable services shall submit an excise tax return, in the approved form and in the prescribed manner, for each calendar month not later than 30 days of the succeeding month, whether or not any excise tax is payable for that month.

**37. <u>Payment of Excise Tax</u>**

1/ The excise tax payable by a licensed manufacturer in respect of excisable goods removed from a manufacturer's factory during a calendar month shall be paid not later than the 30th day of the succeeding month.

2/ The excise tax payable by a supplier of excisable services in respect of supplies of excisable services made by the supplier during a calendar month shall be paid not later than the 30th day of the succeeding month.

3/ The excise tax payable by an importer in respect of the importation of excisable goods into Ethiopia shall be paid to the Authority ot Tax at the time of importation.

4/ For the purpose of assessing, collecting, accounting and enforcing the payment of excise tax on the importation of goods into Ethiopia, the customs law shall apply as if excise tax were customs duty.

**<u>CHAPTER EIGHT</u>**

**<u>OFFENCES AND ADMINISTRATIVE PENALTIES</u>**

**38. <u>Administrative Penalty</u>**

1/ A person who undertakes an activity referred to in Article 15 (1) (a) and (b) without being licensed to do so shall be liable to a penalty equal to:

www.chilot.me

ሀ) የአዋጁ አንቀጽ ፲፭ (፩) (ሀ) ተፈፃሚ የሚሆንበትን በሚመለከት ፈቃድ ቢሰጠው ኖሮ ሊከፍል ይገባ የነበረውን የኤክሳይዝ ታክስ እጥፍ፣

ለ) የአዋጁ አንቀጽ ፲፭ (፩) (ለ) ተፈፃሚ የሚሆንበትን ሰው በሚመለከት የኤክሳይዝ ቴምብር ሊለጠፍባቸው በሚገባ የኤክሳይዝ ታክስ በተጣለባቸው ዕቃዎች ላይ ሊከፈል የሚገባውን የኤክሳይዝ ታክስ እጥፍ፡፡

፪/ በፈቃዱ ላይ ከተመለከተው ቦታ ውጭ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች በማምረት ተግባር ላይ የተሠማራ የተፈቀደለት አምራች በዕቃዎቹ ላይ ሊከፈል የሚገባውን የኤክሳይዝ ታክስ እጥፍ የገንዘብ ቅጣት እንዲከፍል ይገደዳል፡፡

፫/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፰ (፩) የተደነገገው ተፈፃሚ በሚሆንበት ሁኔታ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ከኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር ውጭ ከፋብሪካው ወጪ እንዳደረገ የሚቆጠር የተፈቀደለት አምራች በዕቃዎቹ ላይ ሊከፈል የሚገባውን የኤክሳይዝ ታክስ እጥፍ የገንዘብ ቅጣት እንዲከፍል ይገደዳል፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በታክስ አስተዳደር አዋጅ የተጣሉት አስተዳደራዊ ቅጣቶች ለኤክሳይዝ ታክስም ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፡፡

## ፴፱. <u>ከፈቃድ እና ከኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር ጋር የተያያዙ የወንጀል ጥፋቶች</u>

፩/ ማንኛውም ሰው የዚህን አዋጅ አንቀጽ ፲፭(፫)፣ ፲፰(፬)፣ ፳፮(፩)፣ ፳፯(፩)፣ ፴(፯)፣ ፴፩(፪) እና ፴፪ ድንጋጌዎችን ተላልፎ መገኘቱ በፍርድ ቤት የተረጋገጠ እንደሆነ ከ፫ እስከ ፭ ዓመት ለሚደርስ ፅኑ እስራትና ከብር ፶ሺ እስከ ፩፻ሺ በሚደርስ የገንዘብ ቅጣት ይቀጣል፡፡

፪/ የተፈቀደለት አምራች በፈቃዱ ከተመለከተው ሥፍራ ውጭ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች በማምረት ተግባር ላይ መሰማራቱ በፍርድ ቤት የተረጋገጠ እንደሆነ ከ፭ እስከ ፯ ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት እና ከብር ፩፻ሺ እስከ ፪፻ሺ በሚደርስ የገንዘብ ቅጣት ይቀጣል፡፡

a) double the excise tax that would have been payable if the person were licensed in the case of a person to whom Article 15 (1) (a) applies;

b) double the amount of excise tax payable in respect of the importation of excisable goods requiring an excise stamp, in the case of a person to whom Article 15 (1) (b) applies.

2/ A licensed manufacturer who manufactures excisable goods in premises that are not specified on the manufacturer's license as the factory in which the manufacturer is permitted to manufacture the goods shall be liable to a penalty equal to double the excise tax payable on those goods.

3/ If under Article 28 (1) has been applied to deem a licensed manufacturer to have removed excisable goods from excise control, the manufacturer shall be liable to pay a penalty equal to double the excise tax payable on those goods.

4/ Without prejudice to the provision of this Article, the Tax Administration Proclamation shall apply to penalties imposed under this Article.

## 39. <u>Offences Relating to Licensing and Excise Control</u>

1/ Any person who contravenes the provisions of Articles 15(3), 18(4), 26(1), 27(1), 30(7), 31(2), and 32 commits an offence and is liable if convicted to a rigorous imprisonment for a term of 3 to 5 years and a fine of Birr 50,000 to 100, 000.

2/ A licensed manufacturer commits an offence if he manufactures excisable goods in premises that are not specified on the manufacturer's license as the factory in which such manufacture is permitted and is liable to a rigorous imprisonment for a term of 5 to 7 years and a fine of Birr100,000 to 200,000.

www.chilot.me

፫/ የተፈቀደለት አምራች በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፱ (፩) እና ፲፱ (፪) የተደነገገውን ተላልፎ የተገኘ መሆኑ በፍርድ ቤት የተረጋገጠ እንደሆነ ከ፩ እስከ ፫ ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት እና ከብር ፩፻ሺ ባልበለጠ የገንዘብ ቅጣት ይቀጣል፡፡

፬/ ማንኛውም ሰው:-

ሀ) የዚህን አዋጅ አንቀጽ ፳፭ (፫) (ለ) በመተላለፍ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ከኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር ውጭ ከማምረቻው ፋብሪካ ወጪ ያደረገ እንደሆነ፤

ለ) ፈቃድ ሳይኖረው በኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር ሥር ያሉ ዕቃዎች ተከማችተው በሚገኙበት ቦታ የገባ እንደሆነ፤

ሐ) የኤክሳይዝ ታክሱ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ከኤክሳይዝ ታክስ ቁጥጥር ውጭ ባልተፈቀደ መንገድ ከተከማቹበት ቦታ ወጪ በማድረግ፣ ባህሪያቸውን በመለወጥ ወይም የቁጥጥሩን ሥራ በማወክ ረገድ የተባበረ፣ እንደሆነ፣ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋጋጥ ከ፭ እስከ ፯ ዓመት በሚደርስ ፅኑ እሥራትና ከብር ፩፻ሺ እስከ ፪፻ሺ የገንዘብ ቅጣት ይቀጣል፡፡

፭/ በዚህ አዋጅ ከተደነገገው ውጭ የተመረቱ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ወይም የኤክሳይዝ ታክስ ሳይከፈልባቸው ከተመረቱበት ፋብሪካ ወጪ የተደረጉ ዕቃዎችን የገዛ ወይም ሳይፈቀድለት እነዚህን ዕቃዎች የተቀበለ ወይም በይዞታው ሥር ያደረገ ወይም የኤክሳይዝ ታክስ ያልተከፈለባቸውን ዕቃዎች ለሽያጭ በማዋል ተግባር የተሠማራ ማናቸውም ሰው ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከ፫ እስከ ፭ ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት እና ከብር ፩፻ሺ እስከ ፪፻ሺ በሚደርስ የገንዘብ ቅጣት ይቀጣል፡፡

፮/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፱ ስለኤክሳይዝ ቴምብር የተደነገገውን ተላልፎ የተገኘ ማናቸውም ሰው ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከ፪ እስከ ፫ ዓመት በሚደርስ እስራት እና ከብር ፶ሺ እስከ ፩፻ሺ በሚደርስ የገንዘብ ቅጣት ይቀጣል፡፡

3/ A licensed person who fails to comply with Articles 19 (1) and 19 (2) commits an offence and is liable if convicted to a rigorous imprisonment for a term of 1 to 3 years and a fine of not more than Birr100, 000.

4/ A person commits an offence if he or she:

a) removes excisable goods from excise control in contravention of Article 25 (3) (b);

b) enters any place where excisable goods are stored under excise control without authorization;

c) is involved in the unauthorized removal, alteration, or interference with excisable goods under excise control and is liable if convicted to a rigorous imprisonment for a term of 5 to 7 years and a fine of Birr 100, 000 to 200,000.

5/ Any person who buys, or, without proper authority, receives or has in the person's possession, any excisable goods that have been manufactured contrary to the provisions of this Proclamation, or which have been removed from the place where they ought to have been charged with excise tax before such tax has been charged and either paid or secured or engaged in the trading of excisable goods on which the tax has not been paid commits an offence and is liable, if convicted, to a rigorous imprisonment for a term of 3 to 5 years and a fine of Birr100, 000 to 200,000.

6/ Any person who contravenes Article 29 of this Proclamation, which provide about excise stamps commits an offense and is liable if convicted to an imprisonment for a term of 3 to 5 years and a fine of Birr 50,000 to 100,000.

www.chilot.me

**፵. የታክስ አስተዳደር አዋጅ ተፈፃሚነት**

በዚህ አዋጅ ባልተሸፈኑ የኤክሳይዝ ታክስ ወንጀልና አስተዳደራዊ ጥፋቶች ላይ የታክስ አስተዳደር አዋጅ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

## ምዕራፍ ዘጠኝ
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**፵፩. ታክስ ላለመክፈል የሚደረግ ስምምነት**

፩/ በዚህ አዋጅ የተደነገገው ቢኖርም፣ የታክሱ ባለሥልጣን:-

ሀ) የኤክሳይዝ ታክስ ላለመክፈል የሚያስችል ስምምነት የተደረገ መሆኑን፣

ለ) ማናቸውም ሰው ይህንን ስምምነት በመጠቀም የታክስ ጥቅም ያገኘ መሆኑን፣

ሐ) የስምምነቱ ይዘት ሲመረመር፣ የስምምነቱ ዋና ዓላማ ተዋዋይ ወይም ሌላ ማናቸውም ሰው የኤክሳይዝ ታክስ ጥቅም እንዲያገኝ መሆኑን መረዳት የሚቻል ከሆነ፣ የታክሱ ባለሥልጣን ስምምነቱ እንዳልተደረገ በመቁጠር የኤክሳይዝ ታክስ ጥቅም ያገኘው ሰው የኤክሳይዝ ታክሱን እንዲከፍል ሊወስን ይችላል፡፡

፪/ የታክሱ ባለሥልጣን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ከተገለፀው ውሳኔ ላይ የደረሰ እንደሆነ ይህንኑ የሚገልጽ የውሳኔ ማስታወቂያ ታክሱን መክፈል ላለበት ሰው መላክ አለበት፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የታክሱ ባለሥልጣን ውሳኔ ሊሰጥ የሚችለው የኤክሳይዝ ታክስ የመክፈል ግዴታው ከተቋቋመበት ወር የመጨረሻ ቀን ጀምሮ በ፭ ዓመት ጊዜ ውስጥ ነው፡፡

፬/ ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም:-

ሀ) "ስምምነት" በመግባባት የተፈፀመ፣ በግልጽ የተፈፀመ ወይም በትርጉም የሚደረስበት ወይም በሕግ ፊት ተፈፃሚነት ያለው ቢሆንም ባይሆንም ድርጊት፣ ውልን፣ ማመቻቸትን፣ ቃል ኪዳንን፣ ዕቅድን፣ የውሳኔ ሀሳብን ወይም ግዴታ መግባትን ይጨምራል፡፡

ለ) "የታክስ ጥቅም" ማለት:-

**40. Applicability of the Tax Administration Proclamation**

The provisions of the Tax Administration Proclamation shall be applicable on Excise Tax offences and penalties that are not provided under this Proclamation.

## CHAPTER NINE
## MISCELLANEOUS PROVISIONS

**41. Tax Avoidance Schemes**

1/ Notwithstanding the provisions of this Proclamation, if the Authority of Tax is satisfied that:

a) a scheme has been entered into or carried out exsise Tax;

b) a person has obtained a tax benefit in connection with the scheme;

c) having regard to the substance of the scheme, it would be concluded that the person, or any other, who entered into or carried out the scheme did so for the sole or main purpose of enabling the person to obtain the tax benefit, the Authority may determine the excise tax liability of the person who obtained the tax benefit as if the scheme had not been entered into or carried out.

2/ If a determination is made in accordace with Sub-Article (1) of this Article, the Authority shall issue an assessment giving effect to the determination.

3/ A determination in accordace with Sub-Article (1) of this Article shall be made within 5 years from the last day of the month in which the excise tax liability arose.

4/ In this Article:

a) "scheme" includes a course of action, or an agreement, arrangement, promise, plan, proposal, or undertaking, whether express or implied, and whether or not legally enforceable.

b) "tax benefit" means:

www.chilot.me

(፩) የኤክሳይዝ ታክስ ከመክፈል ግዴታ ነፃ መሆንን ጨምሮ ሊከፈል የሚገባውን የኤክሳይዝ ታክስ መጠን መቀነስ፤

(፪) የኤክሳይዝ ታክስ ተመላሽ የማግኘት መብትን ማቋቋም፤

(፫) የኤክሳይዝ ታክስ የመክፈል ግዴታ የሚፀናበትን ቀን ማዘግየት፤

(፬) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልበትን ቀን በማዘግየት ሌላ ማናቸውንም ጥቅም ማስገኘት፤

(፭) ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የሚያስገኝ ጥቅም:-

ሀ) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ታክሱ የማይከፈልባቸው እንዲሆኑ ማድረግ፤

ለ) የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸው ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች አነስተኛ የኤክሳይዝ ታክስ እንዲከፈልባቸው ማድረግ፤

## ፵፪. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም የሚያግዝ ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፪/ ሚኒስትሩ ለዚህ አዋጅ እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ለሚወጣ ደንብ አፈፃፀም መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## ፵፫. የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች

፩/ በዚህ አዋጅ ምዕራፍ ፫ ክፍል ፩ ፈቃድ ስለማውጣት የተደነገገው ቢኖርም የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች በማምረት ወይም አገልግሎት በመስጠት የተሠማራ ማናቸውም ሰው ፈቃድ ባይኖረውም ወይም ባይመዘገብም ይህ አዋጅ ከወጣበት ቀን አንስቶ እስከ ፮ ወር ድረስ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች የማምረት ወይም ወደአገር ውስጥ የማስገባት ወይም አገልግሎት የመስጠት ሥራ ማከናወን ይችላል፡፡

፪/ ይህ አዋጅ ከፀናበት ቀን በፊት በተመረቱ የኤክሳይዝ ታክስ ባልተከፈለባቸው ዕቃዎች ላይ የኤክሳይዝ ታክስ የሚሠላውና የሚሰበሰበው በዚህ አዋጅ መሠረት ይሆናል፡፡

(1) a reduction in the liability of a person to pay excise tax, including a reduction of the liability to zero;

(2) an entitlement to a refund of excise tax;

(3) a postponement of a liability for the payment of excise tax;

(4) any other advantage arising to the person because of a delay in payment of excise tax;

(5) anything that causes:

a) excisable goods not to be excisable goods or excisable services not to be excisable services;

b) excisable goods or excisable services to be subject to a lower rate of excise tax.

## 42. Regulation and Directive

1/ The Council of Ministers may issue Regulation for the better carrying out of the provisions of this Proclamation.

2/ The Minister shall issue directives for the proper implementation of this Proclamation and Regulation to be issued in accordance with Sub-Article (1) of this Article.

## 43. Transitional Provisions

1/ Notwithstanding Chapter 3 Part 1 of this proclamation, which provides about licensing, persons engaged in the manufacture of excisable goods and provision of services may continue to do so for 6 months from the date of issuance of this Proclamation without having the license.

2/ Excise tax shall be assessed and collected in accordance with this Proclamation on excisable goods produced before the enactment of this Proclamation on which excise tax is not paid.

www.chilot.me

፫/ ይህ አዋጅ ከጸናበት ቀን በፊት የባንክ ፈቃድ በተሰጣቸውና አዋጁ ሥራ ላይ ከዋለበት ቀን አንስቶ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ወደ አገር በሚገቡ ዕቃዎች ላይ የኤክሳይዝ ታክስ የሚጣለውና የሚሰበሰበው በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር ፫፻፯/፲፱፻፺፭ (እንደተሻሻለ) ድንጋጌዎች መሰረት ይሆናል፡፡"

፬/ ይህ አዋጅ ከፀናበት ቀን በፊት መሰብሰብ ሲኖርበት ያልተሰበሰበ የኤክሳይዝ ታክስ በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር ፫፻፯/፲፱፻፺፭ (እንደተሻሻለ) ድንጋጌዎች መሠረት ይሰበስባል፡፡

**፵፬. <u>የተሻሩና ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጎች</u>**

፩/ የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ፫፻፯/፲፱፻፺፭ (እንደተሻሻለ) ተሽሮ በዚህ አዋጅ ተተክቷል፡፡

፪/ ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሕግ፣ መመሪያ ወይም አሠራር ይህንን አዋጅ በሚመለከት ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

**፵፭. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከጸደቀበት ከየካቲት ፮ ቀን ፪ሺ፲፪ ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ መጋቢት ፰ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም**

**ሳህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

3/ Excise tax on goods to be imported into Ethiopia, for which Letter of Credit has been opened prior to the enactment of this Proclamation, and imported with in six months since the proclamation came in to force shall be assessed and collected in accordance with the Excise Tax Proclamation N0. 307/2002 (as amended).

4/ Excise tax due prior to the enactment of this Proclamation shall be assessed and collected in accordance with the Excise Tax Proclamation No. 307/2002. (as amended)

**44. <u>Laws Repealed and Not applicable</u>**

1/ The Excise Tax Proclamation No.307/2002 (as amended) is hereby repealed and replaced by this Proclamation.

2/ Any law, directive or procedure which is not consistent with this Proclamation shall not be applicable on matters provided by this Proclamation.

**45. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall enter into force on the date of its ratified 13th day of February 2020 by House of People's of Representatives.

**Done at Addis Ababa this 17th day of March 2020**

**SAHLEWORK ZEWDIE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

www.chilot.me